የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# መሠረተ ሃይማኖት

እና

# የካህናት ተልእኮ

ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ/ም

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

ሰንበት ረታና ቤተሰቢ ዮገ ቤተ መጻሕፍት

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

## መሠረተ ሃይማኖት ፤

በሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

ተዘጋጀ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ቅዱስ ሲኖዶስ
የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ
በትምህርተ አበ ነፍስ (ፓስተራል ኬር) አገልግሎት
ክፍል ተዘጋጀ ።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## ይዘቶች

| ይዘቶች | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | ፱—፲ |
| መግቢያ ፤ | ፲፩—፲፪ |
| ፩. የእግዚአብሔር መኖር (ህልዎት) | ፲፫—፲፯ |
| ሀ/ ስለ እግዚአብሔር መኖር ማስረጃዎች | |
| ፩/ ሥነ ፍጥረት | |
| ፪/ ሥነ ምግባር (ሕሊና) (ሞራል) | |
| ፫/ ታሪክ | |
| ለ/ የእግዚአብሔር ጠባይዓት | |
| ፩/ ዘለዓለማዊነቱ | |
| ፪/ ሁሉን ቻይነቱ | |
| ፫/ ሁሉን ዐዋቂነቱ | |
| ፬/ ምሉዕ በኵለሄነቱ | |
| ፭/ ቅድስናው | |
| ፮/ ጻድቅነቱ | |
| ፯/ ፍቅር መሆኑ | |
| ፪/ ምሥጢረ ሥላሴ | ፲፯—፲፰ |
| ፫/ ሥነ ፍጥረት | ፲፰—፲፱ |
| ፬/ የእግዚአብሔር መግቦት | ፲፱—፳ |
| ፭/ መላእክት | ፳—፳፩ |
| ፮/ ሰይጣናት | ፳፩ |
| ፯/ የሰው ተፈጥሮና አወዳደቁ | ፳፪—፳፬ |

www.ethiopianorthodox.org

፩/ ተፈጥሮው

፪/ አወዳደቁ

፰/ ምሥጢረ ሥጋዌ . . . . . . ፳፬—፳፭

፱/ የክርስቶስ ሕማም ሞት ፣ ትንሣኤና ዕርገት . . . ፳፮—፳፰

፩/ ሕማሙ

፪/ ሞቱ

፫/ ትንሣኤው

፬/ ዕርገቱ

፲/ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ . . . ፳፰—፴

፲፩/ ቤተ ክርስቲያን . . . . . . ፴—፴፪

፲፪/ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን . . . . ፴፪—፵፯

፩/ ምሥጢረ ጥምቀት

፪/ ምሥጢረ ሜሮን

፫/ ምሥጢረ ቊርባን

፬/ ምሥጢረ ክህነት

፭/ ምሥጢረ ንስሐ

፮/ ምሥጢረ ተክሊል

፯/ ምሥጢረ ቀንዲል

፲፫/ ትንሣኤ ሙታን ፣ የክርስቶስ ዳግም ምጽአትና የመጨረሻው ፍርድ. . . . . . . ፵፰—፶፪

፩/ ትንሣኤ ሙታን

፪/ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት


# መ ቅ ድ ም

በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ኅብረተሰቡን በትምህርተ ሃይማኖትና በምግባረ ሠናይ ለማገልገል ለሚያደርጉት ጥረት ለሥራቸው መቃናት ይረዳል ተብሎ ይህ አነስተኛ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት ፣ ታሪካዊት ፣ ሐዋርያዊትና ፣ ብሔራዊት እንደመሆኗ በየጊዜው ለሕያው እግዚአብሔር ክብርና ለሰዎች ደኅንነት ፣ እኩልነት ስለሕያዋንና ስለሙታን፣ በምርኮ ስላሉትና መሪር በሆነ አገዛዝ ስለተያዙት ፣ ስለተከፉና ስለተሰደዱ እግዚአብሔር አምላካችን ምሕረቱንና ቸርነቱን እንዲያደርግላቸው፣ ስለዝናመ ምሕረት ፣ እክለ በረከትና ስለመሳሰሉት ዘወትር ትጸልያለች ታስተምራለች ፤ በዚህ ዓለም እግዚአብሔርን ከማመስገን ፣ ሰዎችንም ከመርዳት የበለጠ ቅዱስ ተግባር የለም ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ በሕይወታቸው የተቸገሩትን የተጨቆኑትን ቀርቦ የሚያይና የሚመለከት አበ ነፍስ አገልግሎት ሰጭ ክፍል አለው ፤ በዚህ ክፍል አማካኝነት መምሪያው ተገቢውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ይሰጣል ፤ ትምህርተ አበ ነፍስ በሌላ አነጋገር ኖላዊ (ፓስተራልኬር) ተብሎ ይጠራል ፤ ኖላዊ (ፓስተር) ማለት ጠባቂ ነው ፤ የተገኘውም ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው ፤ መዝ ፡ ፳፪ ፡ ፩—፯ ሕዝቅ ፡ ፴፬ ፡ ፩—፲ በመጽሐፍ ቅዱስ ቤተ እሥራኤል የእግዚአብሔር መንጋ ሲባሉ ካህናትና ነቢያተ እግዚአብሔርም ጠባቂዎች ተብለዋል ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም እረኛ እኔ ነኝ ይላል ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፩—፲፮ ። እንዲሁም ጴጥሮስን በጎቼን ጠብቅ አለው ዮሐ፡ ፳፩፡ ፲፭—፲፯ ።

ጴጥሮስም ይህ ቃል ትዝ እያለው በመልእክቱ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን መንጋ ቀሳውስትን እረኞች አድርጎ ይናገራል፤ ፩ኛ ጴጥ ፭፡፩—፬ ። መጠበቅ ማለት መመገብ ፣ መምራት ፣ መገሠጽ ፣ ከአውሬ መጠበቅ ማለት ነው ፤ ይህ ሁሉ የአበ ነፍስ ሥራ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ መምሪያው «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና የካህናት ተልእኮ» በሚል ርእስ ይህን መጽሐፍ ያዘጋጀበት ምክንያት ፤

፩ኛ/ በመጀመሪያ ደረጃ ካህናቱ ስለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ጠንቅቀው በማወቅ ለሐዋርያነት ሥራቸው እንዲረዳቸው ፤ ሐዋርያት ከሦስት ዓመታት በላይ የመምህራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱንና ተአምራቱን ካዩና ከተመለከቱ እንዲሁም ከተረዱ በኋላ ነው ፤ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ በአብ ፤ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው የተባሉ (ማቴ ፥ ፳፰ ፥ ፲፱ ) ።

፪ኛ/ በአምላካዊ ትእዛዝ መሠረት ካህናት ለሐዋርያዊ ተልእኮ ለስብከተ ወንጌል ተግባር እንዲፋጠኑና መንፈሳዊ ግዴታቸውንም በሚገባ እንዲወጡ ይረዳቸው ዘንድ መምሪያው ይህን መጽሐፍ በማዘጋጀት ለአገልግሎት አቅርቧል ።



## መ ግ ቢ ያ

ሃይማኖት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በመገለጡ የተገኘ ነው ፤ ሰው ምንም እንኳ የማምለክና የማመን ጠባይዕ ቢኖረውም እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ራሱን ባይገልጥለት ኖሮ የቀናውን የሃይማኖት ጎዳና እንደማያገኝ የታወቀ ነው ፤ እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በምሳሌው መፍጠሩ እንዲያመልከውና እንዲያምነው እንዲያመሰግነውም ስለሆነ ይህ ለሰው የተደረገ ልዩ አምላካዊ ስጦታ ነው ፤ በመሆኑም ሃይማኖት የአምላክ ስጦታ መሆኑን ያረጋግጣል ።

ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላም እግዚአብሔር ተገልጦ ከውድቀቱ እንደሚያነሣው ተስፋውን ነገረው ፤ በኋላም በየጊዜው በራእይና በሕልም በተአምራትም በተለያየ መልክ ተገልጦ ሰዎች ወደ እርሱ የሚቀርቡበትን መንገድ አሳያቸው በመጨረሻም የባሕርይ ልጁ በሥጋ ተገልጦ «ወደ እኔ ኑ በእኔ እመኑ ፤ በአባቴም እመኑ» በማለት በአስተማራቸው ጊዜ ሃይማኖትን ገልጦላቸዋል ፤ (ማቴ ፥ ፲፩፥ ፳፰) ዮሐ ፥ ፲፬ ፥ ፩ ፤ )ስለዚህ ሃይማኖት በሥነ ፍጥረት በነቢያት በመጻሕፍት ኋላም በአንድ ልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሆነው የእግዚአብሔር መገለጥ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል ።

የትምህርተ ሃይማኖት ምንጮች ሁለት ናቸው ፤ እነሱም ቅዱስ መጽሐፍና ትውፊት ናቸው ፤ እግዚአብሔር ለሰዎች የተናጋሪውና ያደረገው ሁሉ በእነዚህ በሁለቱ ምንጮች ይገኛል ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና ቅዱስ መጽሐፍ ፹፩ መጻሕፍትን ይዞአል መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈና ምንም ስሕተት የሌለበት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ቤተ ክርስቲያናችን ታምናለች ።
፪፥ ጢሞ ፥ ፫ ፥ ፲፮—፲፯ ፤ ፪፥ ጴጥ፥ ፩ ፥ ፳—፳፩ ።

ትውፊት ማለትም ጌታም ሐዋርያትም ተናግረውት በመጽሐፍ ያልተጻፈ ነገር ግን ከቃል ወደ ቃል ሲያያዝ የመጣ ማለት ነው ፤ የቃሉ ትክክለኛ ትርጉም ቅብብል ማለት ነው ፤ (ተውፈየ ተቀበለ ካለው የተገኘ ቃል ነው) ።



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ያስተማረው ትምህርትና ያደረገው ተአምራት ሁሉ በሙሉ በሐዲስ ኪዳን አለመመዝገቡ ተገልጦአል ፤ ዮሐ ፡ ፳፩ ፡ ፳፭ ፤ ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል « አሁንም ወንድሞቼ ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ ፤ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ትውፊት ያዙ» ፪፡ ተሰ፡ ፪፡ ፲፭ ፤ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሊቃውንትም በጉባኤ የወሰኑት ትምህርተ ሃይማኖት በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም አብዛኛው በቃል ተጠብቆ ከቆየው የተወረሰ ነው ። ሐዲስ ኪዳን ቅሉ የተጻፈ ጌታን ከሰሙት ቅዱሳን ሰዎች አፍ እየተነገረ ነው ፤ ስለዚህም ቅዱስ መጽሐፍና ትውፊት ለትምህርተ ሃይማኖታችን እውነተኛ ምንጮች ናቸው ፤ ከእነዚህ ከሁለቱ ምንጮች የተቀዳ ትምህርተ ሃይማኖትም አይለወጥም፤አይሻሻልም ፤ እንዳለ ተጠብቆ ይኖራል እንጂ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት በእነዚህ በሁለቱ መሠረቶች ላይ የተገነባ ነው ፤ ከዚህም ጋር በ፫ ጉባኤያት በኒቅያ (፫፻፳፭) ፤ በቍስጥንጥንያ (፫፻፹፩) ፤ በኤፌሶን (፬፻፴፩) የተወሰነውን የሃይማኖት ቀኖና ቤተ ክርስቲያናችን ትቀበላለች ።

የቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ እምነት በተለያየ ርእስ በተለይም «አምስቱ አዕማደ ምሥጢር» በሚል ርእስ በየጊዜው በልዩ ልዩ የአቀራረብ ዘዴ በሊቃውንት መምህራን እየተዘጋጀ ቀርቦአል ፤ ይህም «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት» በሚል ስያሜ የቀረበው ዝግጅት ከይዘቱና ከአቀራረብ ዘዴው በቀር « በከመ መሀሩነ አበው ቀደምት የቀደሙት አባቶቻችን እንደአስተማሩን » ትምህርተ ሃይማኖት ነው ፤ በቀደሙት አባቶቻችን መምህራን መሠረት ላይ ታንጸናልና ከእነርሱ የሰማነውን እናስተምራለን ።



## ፩. የእግዚአብሔር መኖር (ህልዎት)

የማይታይና የማይመረመር ሁሉን ማድረግ የሚችል ሁሉን የፈጠረ መጀመሪያ ያልነበረው መጨረሻም የማይኖረው ለዘለዓለም የሚኖር አንድ አምላክ መኖሩን ማመን ለሰው ልጆች መሠረታዊ ነገር ነው ።

የሰው ልጅ ስለእግዚአብሔር ያለው ዕውቀት ሁለት ዓይነት ነው ፤

፩ኛ. ሰው በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ስለተፈጠረ በተፈጥሮ የተሰጠው ዕውቀት እያደገ ሲሄድ ፈጣሪውን ተመራምሮ የማወቅ ችሎታ አለው ።

፪ኛ. ሰው ፈጣሪውን ለማወቅ በተፈጥሮ ያገኘው ዕውቀት ቢኖረውም በተጨማሪ በእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ ፈጣሪውን ያውቃል ፤ ይሁን እንጂ ሰው ስለእግዚአብሔር ያለው ዕውቀት የተወሰነ ነው ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የማይመዘንና የማይለካ በመሣሪያም የማይመረመር ስለሆነ ነው ፤ የሰውም ዕውቀት እጅግ የተወሰነ በመሆኑ ነው ፤ ሰው በዓይኑ አይቶና በእጁ ዳስሶ በመሣሪያም መርምሮ ማረጋገጥ የሚችለው የተፈጠረውን ግዙፍ ነገር ብቻ ነው ።

### ሀ. ስለእግዚአብሔር መኖር ማስረጃዎች ፤

እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ራሱን ባይገልጥ ኖሮ ሃይማኖት ሊኖር ባልቻለም ነበር ፤ እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች ባያሳውቅ ሰው ስለ እግዚአብሔር የሚያውቀው አንዳችም ነገር አይኖርም ነበር ፤ በመሆኑም ሰው ስለ ፈጣሪው መጠነኛ መረጃ ያገኘባቸው ከራሱ ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጡ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው ።

### ፩. ሥነ ፍጥረት ፤

የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ህልውና (መኖር) ለመረዳት ምርምር ካደረገባቸው ነገሮች ዋናው ሥነ ፍጥረት ነው ፤ ማንኛውም ነገር ያለ ምክንያት አይገኝም፤አንቀሳቃሽ የሌለው ተንቀሳቃሽ የለም ፤ ለምሳሌ ያለ ጠራቢ ወንበር ያለ ሸማኔ ሸማ ያለ አናጢ ቤት ሌላው ሥራ ሁሉ ያለ ሠራተኛ ሊገኝ አይችልም ፤ በዚህም መሠረት ይህ እጅግ ውብና ድንቅ



www.ethiopianorthodox.org

የሆነው ዓለም በውስጡም ያለው ሥነ ፍጥረት ሁሉ ራሱ በራሱ አልተፈጠረም ፤ በአጋጣሚ ወይም በድንገት የተገኘ አይደለም ፤ ከሁሉ በላይ ዐዋቂና ጠቢብ በሆነው በፈጣሪ እግዚአብሔር ተፈጥሮአል ፤ ከመጨረሻዋ ዝቅተኛ የሥነ ፍጥረት አካል ጀምሮ እስከ ታላቁ ፍጥረት ድረስ ያለው ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መኖር ይመራል ፤ ስለዚህም ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ይላል «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ ጠፈርም የእጁን ሥራ ይመሰክራል» ፤ (መዝ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ፤) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረቱ በኩል ለፍጥረቱ መታወቁን ሲያስረዳ የሚከተለውን ይናገራል ፤ «የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘለዓለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል» (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳) ፤ እንግዲህ ይህ የማይለወጥና የማይዛባ የሥነ ፍጥረት ሥርዐት ያለው ዓለም ለእግዚአብሔር መኖር ታላቅ ምስክር ነው ።

## ፪/ ሥነ ምግባር (ሕሊና) ፤ (ሞራል)

ማንም ሰው በውስጡ አንድ መንፈሳዊ ሕግ እንዳለው ያውቃል ፤ እርሱም ሕሊና ነው ፤ ሰው በተፈጥሮ ባገኘው ሥነ ምግባራዊ ዕውቀት ወይም በሕሊናው አነሣሽነት መልካም ይሠራል ፤ ከክፉም ይርቃል ተላልፍ ክፉ ቢሠራም እንኳ ያው ሕሊናው እንዲጸጸት ያስገድደዋል ፤ እንደዚሁም ክፉ የሠራ እንደሚቀጣ መልካም የሠራም ዋጋ እንደሚያገኝ ያውቅ ዘንድ ሰውን ሕሊናው ይወቅሰዋል ፤ ይህ የሚያመለክተው ለጻድቁም ሆነ ለክፉው እንደ ሥራው ዋጋ የሚከፍልና ሳያዳላ በትክክል የሚፈርድ ከሁሉ በላይ የሆነ አንድ አምላክ መኖሩን ነው ፤ ይህንም ለማስረዳት ቅዱስ ጳውሎስ የሚከተለውን ጽፎአል ፤ «ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና ፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸውም የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ ፤» (ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፲፬ - ፲፭) ።

## ፫/ ታሪክ ፤

የአምልኮቱ ሥርዓት ይለያይ እንጂ በዚህ ዓለም ላይ ያለ አምላክ የኖረ ሕዝብ እንደሌለ ታሪክ ያስረዳል ፤ ሰው ፈጣሪውን ለመፈለግ ወደ ላይ ከመመልከት ያቋረጠበት ክፍለ ዘመን ፈጽሞ የለም ፤ ከጥንት ጀምሮ



እስካለንበት ዘመን ያሉት ሕዝቦች ሁሉ አንድ አምላክ ወይም ብዙዎች አማልክትን ማምለካቸው አንድ ፈጣሪ መኖሩን በትክክል ያመለክታል ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የዓለም ሕዝብ ሁሉ በተመሳሳይም ሆነ በተለያየ መንገድ አንድ ፈጣሪ አለ ብሎ ማመኑ ለሕሊናም ለአእምሮም ተስማሚ ሆኖ ተገኝቶአል ፤ በእርግጥ አምላክ ባይኖር ኖሮ የሰውን አእምሮ ወደ አምልኮት የሚስበው ጠባይ እንደማይኖር የታወቀ ነው ።

ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢያት በመጨረሻም በአንድ የባሕርይ ልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ገልጦአል ፤ ይህንም በዕብራውያን መልእክት ፩፡ ፩፡ በተጻፈው ቃል መረዳት እንችላለን ፤ «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን» ይህም የመጨረሻው የእግዚአብሔር መገለጥና መታወቅ ነው ፤ ራሱ እግዚአብሔር ወልድ «እኔን ያየ አብን አየ» በማለት አረጋግጦአልና ። (ዮሐ ፡ ፲፬፡ ፱)

## ለ. የእግዚአብሔር ጠባይዓት

እግዚአብሔር ረቂቅ አምላክ ነው ሰውም እግዚአብሔርን ለማወቅ ያለው ችሎታ እጅግ የተወሰነ ነው ፤ በመሆኑም የእግዚአብሔርን ባሕርይ ወይም ጠባይ ለመመርመር አይችልም ፤ በሥነ ፍጥረት በታሪክና በሕሊና (ሥነ ምግባር) በኩል በተገኘው የመመራመር ዕውቀት እግዚአብሔርን ፈጽሞ ለመረዳት አይበቃም «በዚህ ዓለም ሳለን እግዚአብሔርን የምናውቀው በከፊል ነው፤በወዲያኛው ዓለም ግን ፊት ለፊት እናየዋለን» ይላል ቅዱስ ጳውሎስ (፩ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪) ።

እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ ባሕርዩን ለመመርመር ባንችልም የቀደሙን አባቶች እንዳስተማሩን ስለ እግዚአብሔር ጠባይዕ ይገልጣሉ ከተባሉት ነገሮች አንዳንዶችን ቀጥሎ እንመለከታለን ።

### ፩. እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው

እግዚአብሔር ከጊዜ ውጭ ነው ፤ ማለት ጊዜ ሳይኖር ነበር የጊዜ ፈጣሪ እርሱ ነውና ዘመናትንም አሳልፎ ለዘለዓለም ይኖራል ፤ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊነት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ያስረዳሉ «ተራሮች ሳይወለዱ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ አንተ ነህ» (መዝ ፡ ፹፱፡ ፪ ፤ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፤) እግዚአብሔር ራሱ በራሱ



www.ethiopianorthodox.org

የነበረና ያለ የሚኖርም ስለሆነ ጊዜ አይወስነውም ፤ ጊዜ አይለውጠውም ፤ በጊዜ የሚወሰን ለመገኘቱ ምክንያት ያለው ብቻ ነው ፤ እግዚአብሔር ግን አስገኝ ስለሌለው ጊዜ አይወስነውም።

፪. <u>ሁሉን ቻይ ነው</u>

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው ሁሉን ነገር ማድረግ ይችላል ፤ የሚሳነው ነገር የለም ፤ በወንጌል እንደተጻፈ በሰዎች ዘንድ የማይቻሉ ነገሮች በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላሉ (ሉቃ ፡ ፲፰ ፡ ፳፯፡ ዘፍ ፡ ፲፯ ፡፩ ። ፲፰ ፡ ፲፬) ።

፫. <u>ሁሉን ዐዋቂ ነው</u>

እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል ፤ ከእርሱ የተሰወረ የለም ። ያለፈውን ያሁኑንና የሚመጣውን ያልተነገሩ ሐሳቦችን ቃላትንና ተግባራትን ከመሆናቸው አስቀድሞ በአንድ ጊዜ ያውቃል ፤ ይህንንም ዳዊት «አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ዐውቀህ አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ - - - መንገደቼን ሁሉ ቀድመህ ዐወቅህ» በማለት ያስረዳል ። (መዝ፡፩፻፴፰፡፩-፬)

፬. <u>በሁሉ ሙሉ ነው</u>

እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ምሉዕ ነው ፤ እዚህ አለ ፡ እዚያ የለም ፡ ወይም እዚያ አለ እዚህ የለም አይባልም ፤ ስለክብሩና ስለልዕልናው በሰማይ ይኖራል ፤ ወይም በማይመረመር ብርሃን ውስጥ ይቀመጣል በ.ባልም እግዚአብሔር በቦታ አይወሰንም እርሱ ከዓለም በላይ ፡ በዓለም ውስጥ ፡ ከዓለምም ውጭ ነው ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትም «ወደ ሰማይ ብወጣ ፡ አንተ በዚያ አለህ ፡ ወደ ጥልቁም ብወርድ አንተ በዚያ አለህ» (መዝ ፡ ፩፻፴፰ ፡ ፰ —፲) በማለት ምሉዕ በኩልሄነቱን ያስረዳሉ ።

፭. <u>ቅዱስ ነው</u>

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ፤ ከክፉና ከርኩስ ነገር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ፤ ፍጹም ንጹሕ ልዩና ክቡር ነው ፤ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ፍጥረቱም ቅዱስ እንዲሆን ይፈልጋል ፤ «እኔ ቅዱስ እንደሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ይላል ። (ዘሌዋ ፡ ፲፱ ፡ ፪)



፮. <u>ጻድቅ ነው</u>

እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ማለት እውነተኛ ነው ። የሥነ ምግባር ሕግ እንዲጠበቅ ይወዳል ፤ በጽድቅ ይፈርዳል ፤ ለማንም አያዳላም ፤ ፍርዱ እውነትና ተገቢ ነው ። (ራእ ፡ ፲፮ ፡ ፯)

፯. <u>ፍቅር ነው</u>

«እግዚአብሔር ፍቅር ነው» (፩ ዮሐ፡ ፬ ፡ ፰ ፤) እግዚአብሔር ማንኛውንም መልካም ነገር ለፍጥረቱ ሁሉ ያለንፍገት በልግስና ስለሚሰጥ ፍቅሩ ይገለጣል ፤ በተለይም ለሰው ልጅ ያደረገው ፍቅሩ ወሰን የለውም ፤ «እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለሁሉ ቤዛ አድርጎ እስከመስጠት ድረስ ይህን ዓለም ወድዶታል» (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ፤)ስለዚህ ፍቅሩ ከሌሎች ጠባይዓቱ የበለጠ ነው ።

## ፪. <u>ምሥጢረ ሥላሴ ፤</u>

እግዚአብሔር በባሕርይ በመለኮት በፈቃድ በሥልጣን አንድ ነው ፤ ግን በስም በአካልና በግብር ሦስትነት አለው ፤ የስም ሦስትነት አብ ፡ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነው ።

የአካል ሦስትነት ፡— አብ ፍጹም አካል አለው ፤ ወልድ ፍጹም አካል አለው እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አካል አለው ።

የግብር ሦስትነት ፡— አብ ወላዲ አስራጺ ነው ፤ ወልድ ተወላዲ ነው ፤ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ነው ፤ ስምና ግብር አይፋለሱም ፤ አብ ፡ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይባልም ወልድም አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይባልም ፤ መንፈስ ቅዱስም አብ ወይም ወልድ አይባልም ፤ እንደዚሁም አብ ተወላዲ ሠራጺ አይባልም ፤ ወልድም ወላዲ አሥራጺና ሠራጺ አይባልም ፤ መንፈስ ቅዱስ ወላዲ አሥራጺና ተወላዲም አይባልም ።

ምሥጢረ ሥላሴ በብሉይ ኪዳን ግልጥ ባይሆንም መሠረተ ሐሳቡ በአያሌ ቦታዎች ተጠቅሶአል ።

«እግዚአብሔርም አለ ሰውን በምሳሌያችን ፡ በመልካችን እንፍጠር» (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፮—፳፯ ፤) «እግዚአብሔር አምላክም አለ እነሆ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ»(ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፳፪)«ኑ <u>እንውረድ</u> ቋንቋቸውንም ከዚያ እንደባልቀው»(ዘፍ ፡ ፲፩ ፡ ፯)እንደዚሁም (ኢሳ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ሆሴዕ፡ ፲፪ ፡ ፱፡)



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ያሉት ጥቅሶች ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ናቸው ፤ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ «እኛ» የሚሉት ቃላት ሦስትነትን ያመለክታሉ ፤ ከዚህም ሌላ መዝ፡ ፴፫ ፡ ፮ና የመሳሰሉት ጥቅሶች ለሦስትነቱ ማረስጃዎች እንደሆኑ በሊቃውንት ተጠቅሰዋል ።

በሐዲስ ኪዳን ግን ምሥጢረ ሥላሴ በሰፊው ተብራርቶ ተነግሮአል ፤ (ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ፤ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ፤) ሊቃውንትም ይህን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል መሠረት በማድረግ ምሥጢረ ሥላሴን አሟልተው ፡ አስፍተውና አጉልተው ተርጒመዋል ።

በሦስቱ አካላት መቀዳደምና መበላለጥ የለም ። አብ አባትና አሥራጺ ስለተባለ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም ፤ አይቀድምም ፤ ወልድም ተወላዲ ስለተባለ ከአብ አያንስም ፡ ከመንፈስ ቅዱስም አይበልጥም አያንስም ፤ መንፈስ ቅዱስም ሠራጺ ስለተባለ ከአብና ከወልድ አያንስም ፤ የሦስቱ አካላት አንዋዋር አንድ ነውና ።

የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ለሰው አእምሮ የረቀቀ በግልጽ ማስረጃም ሊረዳ የማይችል በመሆኑ ምሥጢር ተብሎአል ፤ በእርግጥ ልብ ፡ ቃልና እስትንፋስ ፀሐይና እሳት ለእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ምሳሌዎች ሆነው ተነግረዋል ፤ ነገር ግን በእነዚህም የሚሰጠው ማብራሪያ የረቀቀ ነው ፤ ስለሆነም ትምህርተ ሥላሴ ምን ጊዜም ምሥጢር ነው ።

## ፫. ሥነ ፍጥረት ፤

ይህ የሚታየው ዓለምና በውስጡ ያለው ሁሉ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው ፤ ከዚህ ከሚታየው ዓለም ውጭም ሌላ የማይታይ ረቂቅ ዓለም በውስጡም ያሉት ረቂቃን ፍጥረታት በእግዚአብሔር ተፈጥረዋል ፤ እግዚአብሔር ግዙፉንና ረቂቁን ዓለማት የፈጠረ አስቀድሞ ከነበረ ግብር ሳይሆን እምኀበ አልቦ ነው ፤ ሥነ ፍጥረት እምኀበ አልቦ መፈጠሩን ቅዱሳት መጻሕፍት በሰፊው አብራርተው ያስረዳሉ ፤ «ልጄ ሆይ ሰማይና ምድርን በውስጣቸውም ያለውን ሁሉ ትመለከት ዘንድ እግዚአብሔርም ከሌሉበት አምጥቶ እንደፈጠራቸው ታስተውል ዘንድ እለምንሃለሁ» (፪ ፡ መቃብያን ፡ ፯ ፡ ፳፰) ከዚህም ጋር መዝ ፡ ፴፫ ፡ ፱፤ የሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፳፬ ፤ ሮሜ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ፤ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፫ ፤ ጥበብ ፲፩ ፡ ፲፯ ፤ የፍጥረትን እምኀበ አልቦ መፈጠር ያስረዳሉ ።

ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር አንዳችም ነገር አልነበረም ፤ ራሱ እግዚአብሔር በራሱ ብቻ ይኖር ነበር ፤ ፈጣሪ



ማለት ቅሉ አስቀድሞ በምንም ዓይነትና ቅርጽ ሕልውና ያልነበረውን ነገር ወደ መኖር ያመጣ ቅርጽና ዓይነትም ሰጥቶ የገለጠ ማለት ነው ፤ እግዚአብሔር ፍጥረትን መፍጠሩ በባሕርዩ ጒድለት ኖሮበት የሚያስፈልገው ሆኖ አይደለም ፤ እግዚአብሔር ራሱ በራሱ ለመኖር የሚችል ስለሆነ ፍጹም ነው ፤ በመሆኑም ለሕልውናው ሌላ ድጋፍ አያስፈልገውም።

ይሁን እንጂ ፍጥረታት ዓላማ አላቸው ፤ ይኸውም እግዚአብሔርን ማመስገን ነው ፤ መላእክትና ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ እንስሳትና ሌሎችም ሕይወት የሌላቸው ፍጥረቶች ሁሉ እግዚአብሔርን ለማመስገን ተፈጥረዋል ፤ (መዝ ፡ ፩፻፵፰ ፡ ፩—፯) በተለይም ሰው ክብሩን ለመውረስ የተፈጠረ ነው ፤ በጠቅላላ ሥነ ፍጥረት ለእግዚአብሔር ህልውና ምስክር ከመሆኑም በላይ ለሰው ልጅም አገልግሎት እንዲውል ተፈጥሮአል ።

ፍጥረት ሁሉ በ፮ ቀናት ተፈጥሮ መከናወኑን ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል፤ ነገር ግን አንዳንድ ሊቃውንት ይህ ስድስት ቀን ረዥም ዘመንን እንጂ ቀናትን እንደማያመለክት ይናገራሉ ፤ ይሁን እንጂ በኦሪት ዘፍጥረት ፩ ፡ ፩፡ ላይ «ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን»ተብሎ ስለተጻፈ ፍጥረት የተፈጠረበት ጊዜ በቀናት እንጂ በረዥም ዘመናት አይቆጠርም ፤ ስድስት ቀን የተባለው በዘመን ከተተረጐመ ፍጥረት በማዝገም ለውጥ (ኢቮልዩሽን ) አሁን ካለበት ደረጃ ደረሰ ወደሚለው ፍልስፍና ይመራል ፤ ስለዚህ ፍጥረት በስድስት ቀናት ውስጥ ተፈጥሮአል የሚለው ሐሳብ የጸና ነው (ዘጸአ ፡ ፳ ፡ ፱—፲፩ ፤ በየቀኑም የተፈጠሩት ፍጥረታት የተለያዩ ናቸው ፤ በመጀመሪያው ቀን ፰ ፡ በሁለተኛው ቀን ፩ ፤ በሦስተኛው ቀን ፬፡ በአራተኛው ቀን ፫ ፡ በአምስተኛው ቀን ፫ ፡ በስድስተኛው ቀን ፬ ፍጥረታት ተፈጥረዋል ፤ በድምሩ ፳፪ ይሆናሉ (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፩—፴፩) ።

## ፬. የእግዚአብሔር መግቦት

እግዚአብሔር ይህን ዓለም ከፈጠረ በኋላ አልተለየውም ፤ መመሪያ ሕግ በመስጠት ከዓለሙ ርቆ የሚኖር አይደለም ፤ የፈጠረውን ፍጥረት ይመራል ፤ ያስተዳድራል ፤ ዓለም ራሱ በራሱ የተገኘ ሳይሆን በእግዚአብሔር የተፈጠረ እንደ መሆኑ ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ጥበቃና ርዳታ ያስፈልገዋል ።

ዓለም በእግዚአብሔር ተጠብቆ እንደሚኖር ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚከተለው ያስረዳሉ ፤ «በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን ፡ በእርሱም እንኖራለን»(የሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፳፰ ፤) ስለዚህ እግዚአብሔር የፈጠረውን



www.ethiopianorthodox.org

ዓለም ቸል አይለውም ሁል ጊዜ ይመለከተዋል ፤ ይጠብቀዋል ፤ መጠበቅም ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ፍጡር ወደ ተፈጠረበት ዓላማ እንዲያደርስ ይመራዋል ፤ ይህም የሰውን ነፃ ፈቃድ አይቃወምም ።

## ፫. መላእክት

ከዚህ በፊት እንደገለጥነው እግዚአብሔር የሚታይና የማይታይ ሁለት ዓለማትን ፈጥሮአል ፤ በሚታየው በግዙፉ ዓለም በተፈጥሮው ነፃ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲኖር በማይታየው በረቂቁ ዓለም ደግሞ እንደ ሰው ሙሉ ነፃ ፈቃድ ያላቸው መንፈሳውያን (ረቂቃን) መላእክት ይኖራሉ ይህንም መረዳት የተቻለው በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መላእክት በራእይ መገለጣቸው በታወቀ ጊዜ ነው ፤ መላእክት ከግብር (ማቴሪያል) የተፈጠሩ አይደሉም ፤ ነገር ግን በመዝሙረ ዳዊት ፻፫ ፡ ፬ «መላእክቱን መናፍስት ፡ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ እርሱ ነው » የሚለውን በመመልከት ተፈጥሮአቸው ከእሳትና ከነፋስ ነው የሚሉ አሉ ፤ ይህንም የኢትዮጵያው መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ ፲፫ ፡ ፲፭ ሲያስረዳ እንዲህ ይላል «ከእሳትና ከነፋስ የፈጠራቸው እርሱ እንደሆነ ስላወቁ መላእክት በትሑት ልቡና ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ ፤ » መላእክት መቼ እንደተፈጠሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተመዘገበው የሥነ ፍጥረት ታሪክ ውስጥ አልተጠቀሰም ፤ ይሁን እንጂ በመጀመሪያው ቀን እንደተፈጠሩ በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ይታመናል ፤ መላእክት የማይሞቱ ሕያዋን ናቸው(ሉቃ ፡ ፳ ፡ ፴፮ ) - መላእክት ጾታ የለሽ ናቸው ፤(ማር ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ፤) መላእክት በፍጥረታቸው ረቂቃን መልካቸውም ይህን ይመስላል ሊባል የማይቻል ሲሆን ሥዕላቸው በምልክት ይገለጣል ፤ ሲገለጡም አንዳንድ ጊዜ በሰው መልክ ይታያሉ ፤ ባለ ክንፍ፡ክንፍ የሌላቸውም ሆነው ይታያሉ (ማር ፡ ፲፮ ፡ ፭፡ ሉቃ ፳፬ ፡ ፬ ፡ ኢሳ ፮ ፡ ፪ ፤ ሕዝ ፡ ፩ ፡ ፮ ፤ ዳን ፡ ፱ ፡ ፳፩ ፤)የመላእክት ቊጥር የማይወሰን እጅግ ብዙ ሲሆን በስም የሚታወቁ ጥቂቶች ናቸው ፤ ሚካኤልና ገብርኤል በብሉይና በሐዲስ ተጠቅሰዋል፤(ዳን ፱ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ። ፩ ፡ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፱፡ ይሁዳ ፱ ፤) ከእነዚህም ሌላ ሩፋኤል ዑራኤል ራጉኤል ፋኑኤል በጦቢትና በሄኖክ መጻሕፍት ተጠቅሰዋል ።

### ግብራቸው (ሥራቸው)

መላእክት ስማቸው እንደሚያመለክተው ሥራቸው ተልእኮ ነው ፤ ከእግዚአብሔር ወደ ሰዎች ለምሕረትም ለመዓትም ይላካሉ (ሉቃ ፡ ፩ ፡



፲፱—፳፯) ባለማቋረጥ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ ፤(መዝ ፩፻፵፰ ፡ ፪ ዳን ፡ ፫፡ ፶፰) ድኅነት የሚገባቸው የሰው ልጆችን ሁሉ ይጠብቃሉ፤ (ዕብ፡ ፩ ፡ ፲፬ ፤ መዝ ፡ ፺ ፡ ፲፩፤) ክፉዎችን ይቃወማሉ (ራዕ ፡ ፲፪ ፡ ፯፤)የቅዱሳንን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ(ራእ ፡ ፰ ፡ ፫—፬ ፤)የምእመናንን ነፍሳት ወደ ዕረፍት ይወስዳሉ፤ (ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፳፪፤) የእግዚአብሔርን አገልጋዮች በማናቸውም ችግራቸው ጊዜ ይረዳሉ (የሐዋ፡ ፭ ፡ ፲፱ ፤ ፲፪፡ ፯ ፤) ለእያንዳንዱ ሰው ጠባቂ መልአክ ሆነው ይጠብቃሉ ፤ ሰው ክፉም ሆነ ደግ ቢሠራ ይመሰክራሉ(ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፤) በፍርድ ቀን ከጌታ ጋር ይመጣሉ፤ ያን ጊዜም አገልግሎት ይሰጣሉ (ማቴ፡ ፳፭ ፡ ፫ ፤ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፬፡ ፲፯ ፤) በጠቅላላ መላእክት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መልእክተኞች መሆናቸው በቅዱሳት መጻሕፍት የታወቀ ነው ።

## ፬. ሰይጣናት

እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም እንደሆነ በዘፍጥረት እንረዳለን ፤ ነገር ግን መላእክት ሁላቸው መልካም ተፈጥሮታቸውን አልጠበቁም ፤ ከእነርሱ አንዱ ዲያብሎስ በነፃ ፈቃዱ ወደ ክፋት አዘንብሏል ፤ ዲያብሎስ የግሪክ አጠራር ሲሆን በዕብራይስጥ ሰይጣን ይባላል ፤ ትርጒሙም ተቃዋሚ ማለት ነው ፤ መላእክት ወደ ሰይጣንነት የተለወጡት በትዕቢታቸው ነው ፤ እግዚአብሔር ግን እንደ ሌላው ፍጥረት ሁሉ መልካም አድርጎ ፈጥሮአቸው ነበር ፤ (ዘፍ ፩ ፡ ፴፩) ።

ሰይጣን ሁል ጊዜ ሰዎችን ይፈትናል ፤ ወደ ክፉ ይመራል ፤ የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲተላለፉ ያደርጋል ፤ ሰይጣን ወይም ዲያብሎስ «ከመጀመሪያ ጀምሮ ነፍሰ ገዳይ ነው» (ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፵፬) ተብሎ እንደተጻፈ ሰዎችን ይገድላል ፤ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ጠባቂ መልአክን በሚልክበት ጊዜ ሰይጣን ደግሞ የሰውን ሕይወት ለመፈታተንና ለማጥፋት ከሠራዊቱ አንድ አንዱን ይልካል ።

ሰይጣናት ለእግዚአብሔር ስለማይታዘዙ በንስሐ ለመመለስም ስለማይፈቅዱ ካሣም እንዳይከፈልላቸው ባሕርያቸው ተስማሚ ስላይደለ በዘለዓለማዊ ፍርድ ወደ ጨለማ ተጥለዋል፤ (ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፵፩ ፤ ይሁዳ ፡ ፮፡) ምእመናንን የመፈታተን የማሳሳትና የመቃወም ሥራቸው እንዳለ ነው ፤ መልካቸውን እየለዋወጡ ሰዎችን ሲቃወሙ ይኖራሉ ፤ ( ፪፡ ቆሮ፡ ፲፩ ፡ ፲፬ ።)



www.ethiopianorthodox.org

## ፯. የሰው ተፈጥሮና አወዳደቁ

### ፩· ተፈጥሮው

በዚህ በሚታየው ግዙፍ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ እጅግ የከበረና የፍጥረት ሁሉ አክሊል (ቁንጮ) የሆነ ሰው ብቻ ነው ፤ ሰው ሲባል ነፍስና ሥጋ ወይም መንፈስና ሥጋ ያሉት ነው (ማቴ፡ ፲፡ ፳፰ ፤ መክብብ ፡ ፲፪ ፡ ፯፤ ፩ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፫—፭ ፤) አንዳንዶች ሰው ነፍስ መንፈስና ሥጋ ያሉት የሦስት ግብራት ቅንብር እንደሆነ ይናገራሉ ፤ ለዚህም (፩፡ተሰ፡ ፭፡ ፳፫) ይጠቅሳሉ ፤ ይሁን እንጂ ሁለቱ ነፍስና መንፈስ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ እየተለዋወጡ ይገኛሉ እንጂ በአንድነት አይገኙም ፤ ስለሞት በተነገረበት አንቀጽ ሞት አንዳንድ ጊዜ የነፍስና የሥጋ መለየት ሆኖ ተገልጦአል (ዘፍ ፡ ፴፭፡ ፲፰፤ ፩ኛ ነገሥ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩፤) አንዳንድ ጊዜም የመንፈስና የሥጋ መለየት ሆኖ ተነግሮአል ፤ (ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፶) ።

ሰው ረቂቅ ነፍስ ብትኖረውም መልአክ አይደለም ፤ ግዙፍ አካል ቢኖረውም እንስሳ አይደለም ፤ ከመልአክም ከእንስሳም የተለየ ነው ፤ ሥጋዊና መዋቲ በመሆኑ ከመልአክ ይለያል ፤ ነባቢት ፣ ለባዊትና ሕያዊት ነፍስ ያላቸው በመሆኑም ከእንስሳ ይለያል ።

ለመጀመሪያ ጊዜ የሥጋ ተፈጥሮ ከመሬት ሲሆን ነፍስ ግን ከእግዚአብሔር የተሰጠች ናት፤ (መክ ፡ ፲፪፡ ፯) ፤ ከዚያ በኋላ ነፍስ ከእናትና አባት ትከፈላለች እንጂ ሁልጊዜ አትፈጠርም ፤ ከመዝገበ ነፍሳትም አትላክም ።

የሰው ተፈጥሮ «ለይኩን» በሚል ቃል ሳይሆን በእጅ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ፤ ይህም ከፍጥረታት ሁሉ የከበረ መሆኑን ያመለክታል (ኢዮብ፡፲፡፰) የመጀመሪያው ሰው በዕብራይስጥ «አዳም» ይባላል ፤ ይህም ከመሬት መፈጠሩንና የመልኩን ቅላት ያመለክታል፤ በዕብራይስጥ «አዳም» መሬት «አዶም » ቀይ ማለት ነውና ።

ሰው በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ፤ (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፮—፳፯) የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ማለትም ቅርጽና መጠን አይነትም ሳይሆን ዕውቀት ፣ ቅድስና ፣ ሥልጣን የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆኖ በምድር ላይ የፍጥረታት ገዥ መሆን ነፃ ፈቃድ ፣ ነፃ አእምሮና ዘለዓለማዊ ሕይወት ነው ፤ ስለዚህ ክፉም ሆነ መልካም ለመሥራት ለሰው ነፃ ፈቃድ አለው ።



ሰው ከመጀመሪያ ጀምሮ አሁን ባለው መልኩና ቅርጹ ፍጹም ሆኖ የተፈጠረ ነው፤ መጀመሪያ በሌላ መልኩ ከተፈጠረ በኋላ ቀስ በቀስ ዛሬ ካለበት መልክና ቅርጽ ደረሰ የሚለው አስተሳሰብ በክርስትና ሃይማኖት ትምህርታችን ተቀባይነት የለውም፤ ቅዱሳት መጻሕፍትም ሰው ከልዩ ተፈጥሮ ተነሥቶ ከዚህ ደረሰ በማለት አያስተምሩንም ፤ ሰው ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ፍጥረት በያይነቱና በየመልኩ እንደተፈጠረ ዘፍጥረት ያስተምረናል ፤ (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፩—፴፩) ።

ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም ስላይደለ እግዚአብሔር ከአዳም ጐን ሔዋንን ፈጠረለት ሔዋን ማለትም የሕያዋን ሁሉ እናት ማለት ነው የመጀመሪያዋ ሴት ናትና፣(ዘፍ ፡ ፫፡ ፳) ከጐኑ መፈጠርዋ ወንድና ሴት (ባልና ሚስት) አንድ አካል ናቸው ከተባሉበት ምክንያት አንዱን ያሳያል እንደዚሁም የሰው ዘርዕ ሁሉ ከአንድ ምንጭ እንደመጣ ያመለክታል፤ ከዚህ በኋላ የሰው ዘር ሁሉ ከእነዚህ ከሁለቱ ከአዳምና ሔዋን ተገኝቶአል ።

### ፪/ አወዳደቁ ፤

ሰው በተፈጥሮው ነፃ ፈቃድ ያለውና ነፃ ፈቃዱንም ማንም የማይቃወመው መሆኑን ተመልክተናል ፤ ይህ ከሆነ ዘንድ በነፃ ፈቃዱ አመዛዝኖ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰይጣን መታዘዝን መረጠ ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፈ ይህም ኃጢአት ለዘርው ሁሉ ተላልፎአል ፤ በኃጢአት ከወደቀና ከተረገመ ለሰይጣን ተገዥ ከሆነ በኋላ ወልዶአቸዋልና ልጆቹ ሁሉ እንደርሱ ኃጢአተኞች ሆነዋል ፤ (ዘፍ ፡ ፭ ፡ ፫) የአዳም በደል የመጀመሪያ እንደመሆኑ «ጥንተ አብሶ» ሲባል ለሁሉ በመተላለፉ ደግሞ «የውርስ ኃጢአት» እየተባለ ይጠራል ፤ ይህንም ሲያብራራ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ፤ «በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ ፤ በኃጢአትም ምክያት ሞት መጣ ፤ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ - - - » (ሮሜ፡ ፭ ፡ ፲፪) ።

ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ከገነት ወጣ ልጅነቱን አጣ ፣ ጸጋው ተገፈፈ ፣ ንጽሐ ጠባይውም አደፈ ፤ የመጀመሪያው ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቢጠብቅ ኖሮ ለዘለዓለም በሕይወት ይኖር ነበር ነገር ግን የፈጣሪውን ትእዛዝ በመተላለፉ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ፣ ርደተ መቃብርና ርደተ ገሃነም ተፈረደበት (ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ፤ ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፳፫) ።



www.ethiopianorthodox.org

ይሁን እንጂ ሰው እግዚአብሔርን ቢተው እግዚአብሔር ሰውን አልተወውም የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ የባሕርይ ልጁን ልኮ ከመርገምና ከኲነኔ እንደሚያድነው ተስፋ ሰጥቷ ታል (ዘፍ ፫ ፣ ፲፭ ፣ ፲፪ ፣ ፫ ፤ ገላ ፣ ፫ ፣ ፳ )፤ ትንቢትም አናግሮለታል ፤ (ኢሳ ፣ ፯ ፣ ፲፬ ፤ ሚክ ፭ ፣ ፪ )።

## ፳. ምሥጢረ ሥጋዌ

ሰው ከፍጥረት ሁሉ የከበረና የላቀ ሆኖ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ተፈጥሮ በገነት ከኖረ በኋላ ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትእዛዝ በመተላለፉ ከገነት መውጣቱን ጸጋው መገፈፉን ንጽሐ ጠባይው ማደፉን ተመልክተናል ፤ ይሁን እንጂ በተፈጥሮ የተሰጠው ዕውቀቱና ነፃ ፈቃዱ ስላልተለየው እግዚአብሔር በፈታሒነቱ ቢፈርድበትም በመሐሪነቱ እንደሚምረው ስላወቀ በኃጢአቱ ተጸጸተ (ንስሐ ገባ) እግዚአብሔርም በፍርዱ አንጻር ምሕረቱ አለና ንስሓውን ተቀብሎ በእግረ አጋንንት መጠቅጠቁን በመንጸፈ ደይን መውደቁን ተመልክቶ ከሰይጣን ባርነት ከኃጢአት ቁራኛነት ነፃ ያወጣው ዘንድ ፈቀደ ።

ስለዚህም «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ» ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ በፍጹም አካላዊና ባሕርያዊ ተዋሕዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆኖ ተወለደ ፤ ተወልዶም ከኃጢአት በቀር የሰውነትን ሥራ ሁሉ እየሠራ አደገ በሠላሳ ዓመቱ ተጠመቀ፤ በጳንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ታመመ ፣ ሞተ ፣ ተቀበረ ፣ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ ፤ በ፵ኛው ቀን ወደባሕርይ አባቱ በክብር አረገ ። በተነሣ በ~~አምስተኛው~~ ሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ለደቀ መዛሙርቱ ላከላቸው ።

ምሥጢረ ሥጋዌ ረቂቅ ቢሆንም የሰው አእምሮ ሊያስተውለው የሚገባውን ያህል በቅዱሳት መጻሕፍትና በትምህርተ አበው ተገልጦአል ፤ የምሥጢረ ሥጋዌ መሠረቱ «ቃል በቅድምና ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ - - - ያም ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ» የሚለው ነው ፤ (ዮሐ፡ ፩ ፣ ፩—፲፬)፤አበው ሊቃውንትም ይህን የወንጌላዊውን ቃል መሠረት በማድረግ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ አምልተውና አስፍተው ተናግረዋል ፤ ቅዱስ ቄርሎስ ምሥጢረ ሥጋዌንና ተዋሕዶን ሲገልጥ እንዲህ ይላል ፤ «እንደ ተጻፈ ቃል ሥጋ ሆነ በማይመረመርም የተዋሕዶ ምሥጢር አንድ



አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ፤ መለኮትና ትስብእትም እርስበርሳቸው ሳይቀላቀሉ ሳይለያዩም አንድ ሆኑ» (ሃይ፣ ፸፫ ፣ ፲፯ ፣ ፴) ።

ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ሁለት ልደታት እንዳሉት እናምናለን ፤ ፩ኛ/ ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ከአካል ባሕርይ ከባሕርይ የተወለደው ልደት ነው ፤ ፪ኛው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ያለአባት የተወለደው ልደት ነው ።

አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ ሰውም በተዋሕዶ አምላክ ሆነ ፤ የቃል ገንዘብ ለሥጋ ፣ የሥጋም ገንዘብ ለቃል ሆነ ፤ የቃል ገንዘብ ማለት አምላክነት የባሕርይ ምስጋና ቀዳማዊነት ገቢረ ተአምራት ፣ ሕያውነት ለሥጋ ገንዘቡ ሆነዋል ፤ እንደዚሁም የሥጋ ገንዘብ ማለት ትሕትና ድካም መራብ መጠማት ሕማም ሞት ሌሎችም ካሣ የተፈጸመባቸው ግብራት ሁሉ ለቃል ገንዘቡ ሆነዋል ፤ እንደዚሁም ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ዘእምአካል ፣ ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለደው ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ድኅረ ዓለም በሥጋ ወልደ ማርያም መባልን ገንዘብ አደረገ ፤ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን የተገኘው ሥጋም በቃል ወልደ አብ መባልን ገንዘብ አደረገ፤ (መዝ፣ ፹፯ ፥) ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ ፤ ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሐደ ጊዜ በተዋሕዶው ፍልጠት ፣ ቡዓዴ ውላጤና ሚጠት የለበትም ፤ ተዋሕዶው እንደ ነፍስና ሥጋ ነው ፤ ሥጋ ግዘፉን ሳይለቅ ነፍስም ርቀትዋን ሳትለቅ ተዋሕደው አንድ ሰው እንዲባል ቃል ርቀቱን ትቶ ሳይገዝፍ ምልዓቱንና ስፋቱንም ትቶ ሳይወሰን ትስብእትም ግዘፉን ለቆ ሳይረቅ ሳይዋጥና ሳይጠፋ ውሱንነቱንም ለቆ ምሉዕና ስፉሕ ሳይሆን ነው ።

ሥጋ በመለኮት ቢዋጥ ቢጠፋ መለኮት ሊሞት አይችልምና ድኅነት ባልተገኘም ነበር ፤ ይሁን እንጂ በተዋሕዶው ምንታዌ የለበትም ፤ ከተዋሕዶ በኋላ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንጂ ሁለት አካላት ሁለት ባሕርያት ወይም አንድ አካል ሁለት ባሕርያት አሉት አይባልም ፤ እንደዚሁም አንድ ፈቃድና አንድ ግብር እንጂ ሁለት ፈቃዳትና ሁለት ግብራት የሉትም ።

ሥጋ በተዋሕዶ አምላክ ቢሆንም ጥንት አለው ፤ ፍጻሜ ግን የለውም ከአምላክ ጋር ተዋሕዶአልና አለ ፤ ይኖራልም ፤ እንዲሁም ቃል ድኅረ ዓለም ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋና ነፍስን ተዋሕዶ ሰው ቢሆንም ጥንት የለውም ፍጻሜም የለውም የነበረ ያለና የሚኖር ዘለዓለማዊ ነው ፤ ህላዌው (ለፌ እማርያም) ከማርያም ወዲህ አይደለምና ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፱. የክርስቶስ ሕማም ፥ ሞት ፥ ትንሣኤና ዕርገት

፩. ሕማሙ ፡— መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣቱ ስለ ዓለም ቤዛ በመስቀል ላይ ተሰቅሎና ሞቶ ዓለምን ለማዳን ነው ፤ በመሆኑም በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ በሃይማኖታችንም ቀኖና እንደተገለጠ «ስለእኛ ስለ ሰዎች ስለመዳናችን - - - በጳንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ተሰቀለ መከራ ተቀበለ» ሰው መሆኑ በሰውነቱ ሕማምና ሞትን ለመቀበል እንዲችል ነው ፤ በመለኮቱ ሕማም ወይም ሞት የለበትምና ፤ በሃይማኖት ትምህርታችን ክርስቶስ ታመመ መከራ ተቀበለ ሲባል በእውነት ፍጹም ሰው መሆኑንና ሰውነቱ ምትሐት አለመሆኑን ለመግለጥ ነው ፤ ከዚህም ሌላ ሰው በሆነ ጊዜ ከኃጢአት ብቻ በቀር የሰውን ባሕርይ ሁሉ ማለት በሥጋ የመታመም የመድከም የመራብ ባሕርይን ፥ በነፍስ የሁከት የመተከዝ ፥ የመፍራትና የድንጋጤ ባሕርይን ገንዘብ ማድረጉን ለማስረዳት ነው ።

ጌታችን በመስቀል ላይ መከራ መቀበሉና መሞቱ ትንቢቱ ይደርስና ይፈጸም ዘንድ ነው ፤ (ዘዳግ ፳፩ ፥ ፳፫ ፤ ገላ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ፤ ኢሳ ፡ ፶፫ ) ።

፪. ሞቱ ፡— ጌታችን የመጣለት ዓላማና ትንቢቱ ሁሉ መፈጸሙን ዐውቆ «ሁሉ ተፈጸመ» ካለ በኋላ ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በመለኮታዊ ሥልጣኑ ለየ ።

የክርስቶስ ሞት የነፍስና የሥጋ መለየት ነው ፤ በሃይማኖት ትምህርታችን ክርስቶስ ሞተ ባልን ጊዜ ሥጋ ብቻ ሳይሆን መለኮትም «በሥጋ ሞተ» ብለን እናምናለን ፤ የዕሩቅ ብእሲ ሞት ብቻ ሊያድን አይችልምና ፥ (፩. ጴጥ፡፫ ፡ ፲፰ ። )

የክርስቶስ ሞት በእውነት ፍጹም ሰው መሆኑን ያረጋግጣል ፤ ሞቱ ለበደላችን ሁሉ ካሣ (ቤዛ) ነው(ማቴ ፳ ፡ ፳፰ ፤)ሞቱ ሞትን ደምስሶልናል ፤ መድኃኒታችን በመስቀል ላይ ከሞተበት ሰዓት ጀምሮ ሥጋው ፫ መዓልትና ፫ ሌሊት በከርሠ መቃብር ቆይቶአል ፤ ይህም የሚያረጋግጠው ፩ኛ በእውነት መሞቱን ፥ ፪ኛ/ ትንሣኤው እውነተኛ መሆኑን ነው ፤ የተነሣ ፥ ያው የሞተውና የተቀበረው ነውና ፥ ጌታችን በመቃብር ፫ መዓልትና ፫ ሌሊት ቢቆይም ሙስና መቃብር አላገኘውም ፤ (መዝ.፲፭ . ፲ ፥ የሐዋ . ፪ . ፳፯ ፡ ፴፩ ፡ ፲፫ ፡ ፴፬—፴፭ ። )



የክርስቶስ ሥጋው በመቃብር ሳለ ቅድስት ነፍሱ ወደ ሲኦል ወርዳለች ፤ (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፰—፱)፤ ወደ ሲኦል መውረዱ ሥቃይ ለመቀበል አይደለም ፤ በሲኦል ለነበሩ ነፍሳት ወንጌልን ለመስበክና ለማዳንም አልነበረም በሲኦል ያሉ ነፍሳት ለማመንና ንስሓ ለመግባት ዕድል የላቸውምና ፤ ነገር ግን ክርስቶስ ወደሲኦል የወረደው ሰው ሁኖ ለማዳን መምጣቱን ያምኑ ለነበሩ ጻድቃን ብሲት ድል አድራጊነቱን ፥ ነፃ አውጭነቱንና በሲኦል ላይ ኃይል ያለው መሆኑን ለማወጅ እነርሱንም ለማውጣት ነው ፤ (፩፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፰—፳ )።

፫. ትንሣኤው፡— ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተ በሦስተኛው ቀን መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ድንጋይ አንሡልኝ ሳይል በመለኮታዊ ሥልጣኑ ተነሥቶአል ።

ትንሣኤው የነፍስና የሥጋ መዋሐድና በሕይወት ቆሞ መታየት ብቻ አልነበረም ፤ የተነሣው አካል በመስቀል የተሰቀለውና የተቸነከረው ቢሆንም ያው አካል በተሐድሶ ተነሥቶአል፤ምክንያቱም በፈቀደ ጊዜ ይታይ ነበረ እንጂ በቦታ የተወሰነ አልነበረም ፤ በተዘጋ ቤት ይገባ ነበር፤ (ዮሐ፡ ፳ ፡ ፲፱፤) ከሰዎች ፊት ይሰወር ነበር(ሉቃ ፳፬ ፡ ፴፩፤) ከተነሣ በኋላ ምግብ ሲመገብ ቢታይም በምግብ ምክንያት ኃይልን ለመንሣት አልነበረም ፤ (ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፪—፵፫፤) የክርስቶስ ትንሣኤ ከአልአዛርና ከሌሎችም ሰዎች ትንሣኤ የተለየ ነው ፤ የእነዚያ ትንሣኤ በብሉይ ሥጋ ነው፤ ቆይተውም ሞተዋል ፤ እርሱ ግን ዳግም ሞት የለበትም ፤ (ራእ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ፤) ስለዚህም በኩረ ሙታን ይባላል ፤ (፩፡ ቆሮ፡ ፲፭ ፡ ፳ ፤ ቆላ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ።)

የክርስቶስ ትንሣኤበአራቱ ወንጌሎችና በሌሎችም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ ተገልጦአል ፤ ከዚያም አስቀድሞ በትንቢት ተነግሮ ነበር ፤ (ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፰ ፤ መዝ ፡ ፲፭ ፡ ፲ ።)

በክርስቶስ ትንሣኤ ሞትና ሰይጣን ድል ሆነዋል፤(፩፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ፡ ፳ ፤ ሮሜ ፡ ፮፡ ፫—፲፩ ፤ ኤፌ ፡ ፪፡ ፬—፮) የሰው ልጅ ድኅነት ተፈጽሞአል ፤ (ሮሜ ፡ ፬ ፡ ፳፭፤)ትንሣኤው የክብሩና የኃይሉ መገለጫ ነው፤ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፵፪—፵፬ ፤) የእኛንም ትንሣኤ ያረጋግጣል ፤ እርሱ በክብር እንደተነሣ እኛም እንደርሱ በክብር እንነሣለን (፩፡ቆሮ፡ ፲፭፡ ፳—፳፪፤) ትንሣኤው ለክርስትና እምነት መሠረት መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ የሚከተለውን ያስተምረናል «ክርስቶስ ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ነው» (፩፡ ቆሮ፡፲፭፡ ፲፯—፲፰ ) ።



www.ethiopianorthodox.org

፬/ ዕርገቱ፡— ጌታችን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ አንዳንድ ጊዜ እየታየ ለ፵ ቀናት ከቆየ በኋላ በክብር ወደሰማይ ዐረገ ፤ የክርስቶስ ዕርገትና በአብ ቀኝ መቀመጥ የአድኅኖቱ ሥራ ፍጻሜ ነው ፤ ስለ ዕርገቱ ቅዱሳት መጻሕፍት በሰፊው ይናገራሉ ፤ (ሉቃ፡፳፬ ፶—፶፫ ፤ የሐዋ፡ ፩፡ ፱—፲፩፤ ኤፌ፡ ፩፡ ፳፡ ፬፡ ፳—፲፤ ፩፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፲፮፤ ዕብ ፡ ፩ ፡ ፫-፬ ፡ ፲፬ ፮፡፳ ፡ ፱ ፡ ፳፬)፤ «ዐረገ» ማለትም ልዕልናውን ክብሩን ለመግለጥ ነው እንጂ በሰማይ ሲኖር በምድር የለም ለማለት አይደለም ፤ ከዚህም ሌላ ዕርገቱ የጻድቃንን ክብርና ልዕልና ያመለክታል (ኤፌ ፡ ፪፡ ፮፤ ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፳፬ ) ።

ከዐረገም በኋላ «በአብ ቀኝ ተቀመጠ» (ኤፌ ፩ ፡ ፳ ፤ ዕብ ፡ ፲ ፡ ፲፪፤) በቀኝ ተቀመጠ የሚለው አነጋገር ፊደል በፊደል የሚተረጐም ብቻ ሳይሆን ኃይልንና ሥልጣንን ክብርንም የሚያመለክት ነው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀኝና ግራ ፣ ፊትና ኋላ የለምና ፤ ስለዚህ ነ ቢረ የማን ክርስቶስ ግብረ ትስብእትን ከፈጸመ በኋላ እንደገና የሰውነትን ሥራ የማይሠራ ነገር ግን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በክብር መለኮታዊ ሥራውን እየሠራ የሚኖር መሆኑን የሚያስረዳ ቃል ነው ።

## ፲. ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ፤

ድንግል ማርያም ከቤተ ዳዊት የተወለደች ናት ፤ ወላጆችዋም ቅዱሳን ኢያቄምና ሐና ይባላሉ ፤ ከሕፃንነትዋ ጀምራ ለእግዚአብሔር የተሰጠች ስለነበረች በቤተ መቅደስ አደገች ፤ በ፲፭ ዓመት ዕድሜዋ በብሥራተ መልአክ በግብረ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወለደች ።

ቅድስት ማርያም ዘለዓለማዊት ድንግል ናት ፤ ከመፅነስ በፊት በመፅነስ ጊዜ ከመፅነስ በኋላም ድንግል ናት ፤ ከመውለድ በፊት ፣ በመውለድ ጊዜ ፣ ከመውለድ በኋላም ድንግል ናት ፤ ስለዚህም ዘወትርድንግል ወይም ዘለዓለማዊት ድንግል ትባላለች ፤ ስለ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋም ቅዱሳት መጻሕፍትና ሊቃውንት አበው ይመሰክራሉ ፤(ኢሳ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ፤ ሕዝ ፡ ፵፬፡ ፩—፫ ፤ ማቴ ፩ ፡ ፳ ፤ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፴፬፤)«እርሱን አምላክን ከወለደች በኋላ በድንግልና እንደ ወትሮው ኖረች » (ኤፍሬም ፡ ፬ ፡ ፰ ፤)

ቅድስት ማርያም በሥጋ ብቻ ሳይሆን በሐሳብም ድንግል ናት ፤ በሐሳብዋ ድንግል ናት ማለትም ከኃጢአት ፍጽምት ንጽሕት ናት ማለት ነው ፤ በዚህም መሠረት እመቤታችን በሐልዮ በነቢብ በገቢር ማለት በሐሳብም በቃልም በግብርም ኃጢአት የሌለባት ፍጽምት ንጽሕት ናት ፤ ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጣት ጸጋ ነው፤(ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፳፰፤) አንዳንዶች እመቤታችን አድፍ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ ፤ ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም ፤ ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጂ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን አይደለችምና ፤ ካሣ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሣም ከተከፈለላቸው ወገን ናት ፤ ሆኖም እንደ አዳምና ሔዋን የምኞት የመናገርና የገቢር ኃጢአት ፈጽሞ የለባትም ።

ንጽሕት ድንግል ማርያም ክብር ምስጋና የሚገባት (ብፅዕት) ናት ፤ መላእክትም ፣ ሰዎችም አክብረዋታል አመስግነዋታልም ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል «ጸጋን የተመላሽ ሆይ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ የከበርሽ ነሽ» በማለት አመሰግኖአታል ፤ (ሉቃ ፩ ፡ ፳፰—፳፱ ።)

ቅድስት ኤልሳቤጥም እንደ መልአኩ ቃል «አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ - - - የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይገባኛል ? - - - ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት» በማለት አክብራ አመስግናታለች ፤ (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵—፵፪ ።)

ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አክብሮ ይታዘዝላት ይጠነቀቅላት ነበር ፤ (ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፶፩ ፤ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፭ ፤ ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፳፯—፳፰ )።

እርስዋ ራስዋም በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ «ከእንግዲህ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ያከብሩኛል» በማለት ስለራስዋ ክብር ተናግራለች (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵፰—፵፱ )።

ስለዚህ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ ፣ በመዝሙርና በማኅሌት በስብከትም በጸሎትም በጠቅላላ በቤተ ክርስቲያን በሚፈጸመው የአምልኮት ሥነ ሥርዓት ሁሉ ከፍተኛ ክብር አላት ፤ መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ናት ፤ በወርና በዓመት የተለየ የክብር (የበዓል) ቀን ተመድቦ በልዩ ሥነ ሥርዓት ትከብራለች ።

ድንግል ማርያም እመ አምላክ ወይም ወላዲተ አምላክ ተብላ ትጠራለች ፤ (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፴፪ ፤) ክርስዋ በድንግልናዊ ልደት የተወለደው



www.ethiopianorthodox.org

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነውና ከአብ የተወለደው ከቅድስት ማርያም የተወለደው ነው ፤ ከአብ በመለኮታዊ ባሕርይ የተወለደው ከድንግል ማርያም በሰብአዊ ባሕርይ ተወልዶአል ፤ ያው አንዱ ወልደ እግዚአብሔር ከርስዋ በሥጋ ስለ ተወለደ ወላዲተ አምላክ እመ አምላክ ትባላለች ።

ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ካላልናት ከርስዋ የተወለደው ክርስቶስ ሰው ብቻ እንጂ አምላክ አይደለም ያሰኝብናል ፤ ከርስዋ የተወለደውም ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ከሆነ ሊያድነን ባልቻለም ነበር ፤ ስለዚህ ድኅነታችን የተመሠረተው ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ በመሆንዋ ላይ ነው ፤ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ እንደሆነች የማያምን የክርስቶስን አምላክነትም አያምንም ።

ድንግል ማርያም በእግዚአብሔር ዘንድ ከፍተኛ ባለሙዋል ስለሆነች አማላጃችን ናት ፤ እርስዋ ለእኛ የአደራ እናት ናት ፤ እኛም ለእርስዋ የአደራ ልጆች ነን (ዮሐ ፣ ፲፱ ፣ ፳፯—፳፱ ፤ ) ስለዚህ ትማልድልናለች ።

ድንግል ማርያም ከጌታችን የአድኅኖት ሥራ የተለየችበት ጊዜ የለም፤ ክርስቶስ ዓለምን ያዳነው ከርስዋ በነሣው ሥጋ ነውና ፤ ስለዚህም አማላጅነትዋ የታመነ ነው ፤ በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ላይ ተገኝታ «እርሱ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» ማለትዋ ክርስቶስ ለሰዎች ሊያደርገው ያቀደውን ሁሉ የምታውቅና ሰዎች ለክርስቶስ በመታዘዝ እንዲድኑ የምትመራ መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት መሆንዋን ያመለክታል ፤ (ዮሐ ፣ ፪ ፣ ፩ ።

በዚህ መሠረት እመቤታችን ቅድስት ማርያም «ንጽሕት ድንግል ወላዲተ አምላክ» ተብላ እንደምትጠራ ሰአሊተ ምሕረት ለውሉደ ሰብእ ለሰው ልጆች ምሕረት ለማኝ ተብላ ትጠራለች (ኤፍሬም ፣ ፯ ፣ ፩ ።)

ድንግል ማርያም ንጽሕትና ቅድስት መልዕልተ ፍጡራን ብትሆንም በ፷፬ ዕድሜዋ አዳማዊ ሞትን ሞታለች ፤ ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉምና (፩ ቆሮ ፣ ፲፭ ፣ ፶ ፤)ይሁን እንጂ ሙስና መቃብር አላገኛትም ፤ በሞተች በሦስተኛው ቀን በእግዚአብሔር ኃይል ተነሥታ በክብር ዐርጋለች ።

## ፲፩. ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ቃል በቃል ሲፈታ የክርስቲያን ቤት ማለት ነው ፤ ሲተረጐም ግን ክርስቲያኖች ለጸሎት ለአምልኮት የሚሰበሰቡበት ቤት



ማለት ነው ፤ እንደዚሁም አዲስ ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉ ክርስቲያኖችን ያመለክታል ፤ (፩ ፣ ቆሮ ፣ ፮ ፣ ፲፱፤) በተጨማሪም በክርስቶስ የተመሠረተና የተቋቋመ ማኅበረ ምእመናንን የሚያመለክት ቃል ነው ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት የዜማ ድርሰት « - - - አቅሌስያ ቤተ ክርስቲያን ዘንሰምያ» የሚል ንባብ አለ ፤ አቅሌስያን ቤተ ክርስቲያን ለማለት ነው ፤ ቃሉ የግሪክ ነው ፤ ትርጓሜውም የተጠራች የተመረጠች ማለት ነው ፤ እንደገናም ጉባኤ ማለት ይሆናል ፤ ማኅበረ ምእመናንም በክርስቶስ የተጠሩና የተመረጡ ስለሆኑ ይህ ስያሜ ተሰጥቶአቸዋል ፤ (፩፣ ጴጥ፣ ፪፣ ፱—፲ ) ።

የብሉይ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር ፣ ቤተ እስራኤል ነበሩ ፤ በሐዲስ ኪዳን ግን ሕዝበ እግዚአብሔር የሚባሉ ቤተ ክርስቲያን ወይም ማኅበረ ምእመናን ናቸው ፤ የብሉይ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር በደመ እንስሳ የታተሙ ነበሩ ፤ የሐዲስ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር ግን በደመ ክርስቶስ የታተሙ ናቸው ፤ የብሉይ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር ሕግን በሙሴ በኩል ተቀብለዋል ፤ የሐዲስ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር ግን ወንጌልን በቀጥታ ከክርስቶስ ተቀብለዋል ፤ ማኅበረ ምእመናን ወይም ክርስቲያኖች በማኅበረ እስራኤል ስለገቡ ስሙንም ክብሩንም ይዘዋል ።

በክርስቶስ ለተመሠረተችው እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ የተገለጡ አራት መታወቂያዎች አሉአት ።

፩/ ቤተ ክርስቲያን «አንዲት ናት»፤ መሪዋ ራሱ ክርስቶስ አንድ ነውና ፤ በጭቃ በጨፈቃ ፣ በዕብነ በረድ በወርቅና በዕንቍ ብትሠራ ሥርዐተ አምልኮትዋ አንድ ነውና ።

፪/ ቤተ ክርስቲያን«ቅድስት ናት»ክርስቶስ በደሙ ቀድሶአታልና (የሐዋ ፣ ፳፣ ፳፰)፤ ክርስቶስ የሠራላትን ቅዱሳት ምሥጢራት ጠብቃ ምእመናንን እየቀደሰች ማለት እያከበረች ትኖራለችና ፤ ቅዱስ ቃሉን ታስተምራለችና ፤ እንደዚሁም የቅዱስ መንፈስ ማደሪያ ናትና «ቅድስት» ትባላለች (፩፣ቆሮ፣ ፯ ፣ ፲፱፤ ፪፣ቆሮ ፣ ፫ ፣ ፲ ) ፤ ከዚህም ጋር እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ቅዱሳን ከቤተ ክርስቲያን ይገኛሉና ቅድስት ናት ።

፫/ «ኵላዊት» (በሁሉ ያለች) ናት ፤ በግእዝ «እንተ ላዕለ ኵሉ » ተብሎአል ፤ ይህም በዓለም ሁሉ ያለች ማለት ነው ፤ ቤተ ክርስቲያን በዘር በቀለም ሳትወሰን በዓለም ውስጥ ለሚገኙ ለሰው ዘሮች ሁሉ ናት ፤ (ገላ ፣ ፫ ፣ ፳፭—፳፱)፤ ቤተ ክርስቲያን በዘመናት ሁሉ ያለችና የምትኖር ናት፤ (ማቴ፣ ፳፰ ፣ ፳)፤ ቤተ ክርስቲያን በዐጸደ ሥጋና በዐጸደ ነፍስ ላሉትም ሁሉ ናት ።



www.ethiopianorthodox.org

፬/ ቤተ ክርስቲያን «ሐዋርያዊት ናት» ፤ ከክርስቶስ በኋላ በሐዋርያት ትምህርትና ስብከት ተስፋፍታለችና (የሐዋ፡ ፪ ፡ ፵፩ ፤ ኤፌ ፡ ፪፡ ፳ ፤) የሐዋርያትን ትምህርትና ትውፊት ተቀብላ ስታስተምር ትኖራለችና ፤ የመሪዎችዋ የጳጳሳት ሥልጣነ ክህነት ሳይቋረጥ ከሐዋርያት የተያያዘ ነውና ሐዋርያት ወይም የሐዋርያት ጉባኤ ተብላ ትጠራለች ፤ እነዚህን አራቱን መታወቂያ ምልክቶች ያልያዘች ቤተ ክርስቲያን ፡ ቤተ ክርስቲያን አትባልም ።

## ፲፪. ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

ምሥጢር የሚለው ቃል ግሪክ ነው ፤ በግእዝና በአማርኛም እንዳለ ተወስዶአል ፤ ትርጓሜውም የማይታይ ረቂቅ ማለት ነው ፤ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ማለትም በሚታይ ምልክት የማይታይ ጸጋ የሚሰጥባቸው በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙ ሥርዐታት ማለት ነው ፤ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና በግዙፍ ምልክት የሚሠሩ ነገር ግን በእምነት ዐይን ብቻ የሚታዩ ረቂቃን የሆኑ ነገሮች ሁሉ ምሥጢራት ይባላሉ ። ዕርገተ ጸሎት በዕጣን (መዝ ፩፻፵፩ ፡ ፪ ፤ ራእ ፰ ፡ ፫-፬) ፍትሐተ ሙታን በጸሎት (፪ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፯-፲፰) ምሥጢራት ናቸው ፤ በተለይ ምሥጢራት የሚባሉ በጳጳሳት ወይም እውነተኛ ሐዋርያዊ ሥልጣነ ክህነት ባላቸው ቀሳውስት የሚፈጸሙት የማይታይ መለኮታዊ ጸጋ የሚሰጥባቸውና በግዙፍ ምልክት የሚሠሩት ናቸው ።

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በቍጥር ሰባት ናቸው ፤ እነርሱም ጥምቀት ፤ ሜሮን ፡ ቅዱስ ቍርባን ፡ ክህነት ፡ ንስሐ ፡ ተክሊል ፡ ቀንዲል ናቸው ፤ ይኸውም በመጽሐፈ ምሳሌ ፱ ፡ ፩ ላይ በተጠቀሱት አዕማድ ምሳሌነት ነው ፤ እንደዚሁም በትንቢተ ኢሳይያስ ፲፩ ፡ ፩—፪ የተጸፉትን ሰባት ሀብታት ስለሚያሰጡ ነው ፤ በእነዚህም የተለያየ ሀብት መንፈሳዊ ይሰጣል ፤ በጥምቀት መንፈሳዊ ልደት ፡ በሜሮን መንፈሳዊ ዕድገት፡በቅዱስ ቍርባን መንፈሳዊ ምግብ በክህነት ፡ የማስተማር ፡ የመምራትና የመቀደስ መንፈሳዊ ኃይል ፡ በንስሐ መንፈሳዊ ተሐድሶና ስርየተ ኃጢአት ፡ በተክሊል የጋብቻ ጽንዐትና ቅድስና በቀንዲል ሥጋዊና መንፈሳዊ ኃይል ይሰጣል ።

ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ሁሉ የሚያስፈልጉና የማያስፈልጉ አሉ ፤ ጥምቀት ሜሮን ቅዱስ ቍርባንና ንስሐ



ለሁሉም ያስፈልጋሉ ፤ ክህነት ፡ ቀንዲልና ተክሊል ግን ለሁሉም ግድ አያስፈልጉም ።

ከሰባቱ ምሥጢራት መካከል የማይደገሙና የሚደገሙ አሉ ፤ ጥምቀት፡ ሜሮን ፡ ክህነትና ተክሊል አይደገሙም ፤ የቀሩት ግን ይደገማሉ፤ ይልቁንም ይዘወተራሉ ፤ በአንድ ቀን የሚፈጸሙና የማይፈጸሙ አሉ ፤ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ጥምቀት ሜሮንና ቅዱስ ቍርባን ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ቀን ይፈጸማሉ ፤ ሌሎች ግን በሚያስፈልጉበት ጊዜ ይፈጸማሉ ።

ከሰባቱ ምሥጢራት መካከል ክህነት በጳጳስ ብቻ የሚሰጥ ሲሆን ሌሎቹ ግን በጳጳስ ወይም በቀሳውስት ሊሰጡ ይችላሉ ።

## ፩. ምሥጢረ ጥምቀት

ጥምቀት ማለት መጥለቅ ፡ መነከር ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር በውሃ ውስጥ መግባት ማለት ነው ።

ከሰባቱ ምሥጢራት ሁሉ መጀመሪያው ጥምቀት ነው ። ጌታችን «ማንም ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም» ብሎ በተናገረው መሠረት ፡ ጥምቀት ወደ ቤተ ክርስቲያንና ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር መግቢያ በር ነው ፤ (ዮሐ፡፫ ፡ ፭) ያልተጠመቀ የቤተ ክርስቲያን አባል አይሆንምና ፤ ወደ መንግሥተ ሰማያትም አይገባምና ።

ስለ ጥምቀት አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ምሳሌ ተመስሎአል ትንቢትም ተነግሮአል ፤

ምሳሌዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ የኖህ መርከብ ዘፍ ፯ ፡ ፲፯ ፤ ፩ ጴጥ፡፫ ፡ ፳—፳፪ ፡
ለ/ ግዝረት ቆላስይስ ፪ ፡ ፲፩—፲፪ ።
ሐ/ እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን መሻገራቸው ፩፡ቆሮ ፲ ፡ ፩—፲፪ ፤
መ/ ጥምቀተ ዮሐንስ ማቴ፡፫ ፡ ፲፩ ፤ የሐዋ፡፩ ፤ ፭ ፡ ፲፱ ፡ ፩—፲፰ ፤

ትንቢቱም «ከኃጢአታችሁ ትነጹ ዘንድ በንጹሕ ውሃ እረጫችሁ አለሁ» ተብሎ የተነገረው ነው ፤ (ሕዝ ፡ ፴፮ ፡ ፳፭ ።)

### የጥምቀት አመሠራረት

ጥምቀት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተመሥርቶአል ፤ ጌታችን ጥምቀትን በተግባርና በትእዛዝ መሥርቶታል ፤ በተግባር ማለት ራሱ



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆአል ። (ማቴ ፫፡፲፫—፲፯ ፤) በትእዛዝ ማለት ከትንሣኤ በኋላ «ሑሩ ወመሀሩ ኵሎ አሕዛበ ወአጥምቅዎሙ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስም ስም አጥምቋቸው» (ማቴ ፳፰፡ ፲፰—፲፱) ፤ ብሎ ደቀ መዛሙርቱን አዝዞአቸዋል ፤ ነገር ግን በምሥጢረ ጥምቀት የሚገኘው ሙሉ ጸጋ የተሰጠ በአምሳኛው ቀን በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ነው ፤ (የሐዋ ፤ ፪ ፡ ፩-፬ ፤ ፲፱ ፡ ፮) ።

## አፈጻጸሙ

ምሥጢረ ጥምቀት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እውነተኛ ሐዋርያዊ ሥልጣነ ክህነት ባለው ካህን ወይም ጳጳስ የተመደበው ጸሎት ከተደረሰ በኋላ በውሃ ውስጥ በመጥለቅ ይፈጸማል ፤ በመጀመሪያ ጊዜ ዲያቆናት ያጠምቁ ነበር ፤ (የሐዋ ፤ ፰፡ ፴፰ )፤ በኋላ ግን በቄስ ወይም በጳጳስ ብቻ እንዲሆን ተወስኖአል ።

ጥምቀት በውሃ መሆኑ ፦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃ ስለተጠመቀ ነው ማቴ ፫ ፡ ፲፫-፲፯)፤ «ማንም ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር መግባት አይችልም» ስለተባለ ነው (ዮሐ፡፫፡ ፭)፤ሐዋርያትም በውሃ ያጠምቁ ነበር (የሐዋ፡ ፪፡፴፯-፴፰፡ ፰ ፡ ፴፰ )፤ ውሃ መንጽሔ ነው ጥምቀትም ከኃጢአት ያነጻል ውሃ ለሁሉ የሚገኝ ነው ጥምቀትም ለሁሉ የታዘዘ ነው ፤ ተጠማቂው በሚጠመቅበት ጊዜ ፫ ጊዜ በውሃ ውስጥ ብቅ ጥልቅ እንዲል ይደረጋል ፤ ጌታችን እንደዚሁ ተጠምቋልና (ማቴ፡ ፫ ፡ ፲፮ )፤ ሐዋርያትም በዚሁ አይነት ያጠምቁ ነበርና (የሐዋ ፰ ፡ ፴፰ )፤ ከዚህም ሌላ ጥምቀት የክርስቶስ የሞቱና የመቀበሩ ምሳሌ ነውና ምሳሌነቱ እንዲጸድቅ ተጠማቂው ሦስት ጊዜ በውሃው ውስጥ ብቅ ጥልቅ ይላል (ሮሜ ፮ ፡ ፫-፬) ።

## በምሥጢረ ጥምቀት የሚገኝ ጸጋ

በምሥጢረ ጥምቀት የውርስ ኃጢአትና ከጥምቀት በፊት የተሠሩ ኃጢአቶች ሁሉ ይሰረያሉ(የሐዋ፡ ፪ ፡ ፴፰—፴፱ ፤ ፳፪ ፡ ፲፮ ፤ ቆላ ፪ ፡ ፲፪—፲፫ ፤ ፩ ጴጥ ፫ ፡ ፳፩ )፤ መንፈሳዊ ልደትና ሐዲስ ሕይወት ይገኛሉ፤ (ዮሐ ፫ ፡ ፫—፭)፤ ክርስቶስን መምሰል (ገላ ፫ ፡ ፳፯—፳፰) ቅድስና (ንጽሕና) (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፭—፳፯) ፤ ድኅነት (ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፮) ይገኛል ።

ጥምቀት ለሁሉም ነው ፤ ወንድ ሴት ሕፃን ሽማግሌ ካመኑ መጠመቅ አለባቸው ፤ ምክንያቱም በመጀመሪያው ሰው ምክንያት የሁሉም ንጽሐ ጠባይዕ አድፏልና ፤ (ኢዮብ ፲፬ ፡ ፬ ፤ መዝ ፡ ፶፩ ፡ ፭ ፤ ሮሜ ፭ ፡ ፲፪ ፤ ኤፌ ፪ ፡ ፫) ፤ ንጽሐ ጠባይዕ ያደፈባቸው ወይም የጥንተ አብሶ ውርስ ያለባቸው ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይችሉምና (፩ ፡ ቆሮ ፲፭ ፡ ፶ ፤ ራእ ፡ ፳፩ ፡ ፳፯ )፤ በውሃ የሚፈጸም ክርስቲያናዊ ጥምቀት ብቻ ሰውን አዲስ ልደት እንዲወለድ በማድረግ ይህን የጥንተ አብሶ ውርስን ፡ ያስወግዳል (ዮሐ ፫ ፡ ፫—፯ ፤) ስለዚህ ሰው ሁሉ ለመዳን ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ አለበት ።

## ጥምቀት አንዲት ናት

ምሥጢረ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ ነው ፤ አይደገምም (ኤፌ ፬ ፡ ፭) ሥጋዊ ልደት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ መንፈሳዊ ልደትም አንድ ጊዜ ብቻ ነው ፤ የጥምቀት ምሳሌ የሆነው ግዝረት አንድ ጊዜ እንደሆነ ጥምቀትም አንድ ጊዜ ይሰጣል ፤(ቈላ ፪፡ ፲፪ ፤) ጥምቀት በክርስቶስ ሞትና በትንሣኤ ተመስሎአል ፤ ስለዚህ ሞትም ትንሣኤም አንድ ጊዜ እንደ ሆነ ጥምቀትም አንድ ጊዜ ብቻ ይፈጸማል እንጂ አይደጋገምም (ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፬።)

## ጥምቀተ ሕፃናት

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለዱ ወንዶችን በ፵ ቀናቸው ሴቶችን በ፹ ቀናቸው እንዲጠመቁ ትፈቅዳለች ፤ የቀኑ ጉዳይ ከብሉይ ኪዳን የተወረሰ ነው ፤(ዘሌዋ ፡ ፲፪ ፩—፰) እንደዚሁም በመጽሐፈ ኩፋሌ አዳም በተፈጠረ በ፵ ቀኑ ሔዋንም በተፈጠረች በ፹ ቀንዋ ልጅነት እንደተቀበሉ ተገልጦአልና በዚያ መሠረት ወንድ በ፵ ቀኑ ሴት በ፹ ቀንዋ ይጠመቃሉ ፤ (ኩፋሌ ፬ ፡ ፱—፲፪) ።

ለሕፃናት ጥምቀት ያስፈለገበትም ምክንያት የጥንተ አብሶ ውርስ ስላለባቸው ከዚያ ለመንጻት እንዲችሉ ነው ፤ ጌታችንም ወደዚህ ዓለም የመጣው ሁሉንም ማለት ደቂቅን ፤ ሕፃናትን ፡ ወራዙትንና አዕሩግን ፡ ወንዶችና ሴቶችን ለማዳን ነው ፤ ስለዚህም ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ይላል «እደ ወአንስተ ወሕፃናተ ከመ ይቤዙ ተወልደ ፡ ወንዶችንና ሴቶችን ሕፃናትንም ይዋጅ ዘንድ ተወለደ » (ያሬድ ሠለስት)

ከዚህም ሌላ ለጥምቀት ምሳሌ የነበረው ግዝረት ለሕፃናት ይፈጸም ነበር ፤ (ቆላ ፡ ፪ ፡ ፲፩—፲፫) በማየ ዓይኅ የዳኑት ኖኅና ልጆቹ ነበሩ (፩ ጴጥ ፫ ፡ ፳) ቀይ ባሕርን የተሻገሩ ሕፃናትም ነበሩ ፤ (፩ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፩—፪)፤ ተስፋ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ለአበው ብቻ ሳይሆን ለልጆችም ጭምር ነበር ፤ (የሐዋ ፡ ፪ ፡ ፴፰—፴፱) ቅዱሳን ሐዋርያትም ብዙ ቤተሰቦችን ከእነልጆ




www.ethiopianorthodox.org

ቻቸው ያጠምቁ ነበር (የሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፴፫፤ ፩ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ፤ የሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ፤ ፲ ፡ ፵፬—፵፰ ፤ የሐዋ ፡ ፰ ፡ ፭—፲፯)፤ እግዚአብሔር ጸጋውን ለሕፃናት አልነፈገም ፤ ኤርምያስና መጥምቁ ዮሐንስ በሕፃንነታቸው ጸጋውን አግኝተዋል ፤ (ኤር ፡ ፩ ፡ ፭ ፤ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፭) ፤ በእነዚህ ምሳሌዎች መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ሕፃናትን ታጠምቃለች፤ ሕፃናት ያለጥምቀት እንዲሞቱ ማድረግ በክርስቲያን ወላጆች ላይ ታላቅ በደል መሆኑንም ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች ፤ ሕፃናት ከጥንተ አብሶ ውርስ በስተቀር የገቢር ኃጢአት ስለሌለባቸው በሚጠመቁበት ጊዜ ንስሓ አያስፈልጋቸውም ።

የሕፃናት ጥምቀት ፥ በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳሪዎቻቸው ወይም በክርስትና አባትና እናታቸው እምነት ይፈጸማል ፤ የአንዱ እምነትም ሌላውን እንደሚጠቅም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳሪዎቻቸው እምነት ለበሽተኞች ተአምራትን ያደርግና ይፈውሳቸው ነበር ፤ (ማር ፡ ፪ ፡ ፭ ፤ ማቴ ፡ ፰ ፡ ፭—፲፫ ፡ ፲፭ ፡ ፳፪—፳፰) ።

## የተጠማቂው ግዴታ

ተጠማቂው ትልቅ ከሆነ በቅድሚያ ትምህርተ ክርስትናን መማር በሚጠመቅበት ጊዜ እምነቱን ማሳወቅ (ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፮ ፤) ንስሓውን መግለጥ (የሐዋ ፡ ፪ ፡ ፴፰) አለበት ፤ የሚጠመቁት ሕፃናት ከሆኑ ግን በእነርሱ ፋንታ የክርስትና አባትና እናታቸው ሁሉን ነገር ይፈጽማሉ ።

# ፪. ምሥጢረ ሜሮን

ሜሮን ማለት ቅብዐት ማለት ነው ፤ ቃሉ የጽርዕ ነው ፤ በግእዝም ሆነ በአማርኛ እንዳለ ተወስዶአል ፤ ምሥጢረ ሜሮን አዲሱ ተጠማቂ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግና እንዲበረታ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የሚያሰጥ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ነው ፥ ሜሮን ከዘይት (ወይራ) ከበለስና ከተለያዩ ዕፅዋት በጳጳሳት ይፈላል (ይወጣል) ።

## አጀማመሩ

ምሥጢረ ሜሮን ጌታ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን በላከላቸው ጊዜ ተጀምሮአል ፤ (የሐዋ ፡ ፪ ፡ ፩—፬) ፤ ቀጥሎም ቅዱሳን ሐዋርያት ማንኛውንም አማኒ ከአጠመቁ በኋላ በተጠማቂው ራስ ላይ እጃቸውን በመጫን መንፈስ ቅዱስን ያሳድሩበት ነበር ፤ (የሐዋ ፡ ፲፱ ፡ ፭—፯) ፤ ያንጊዜ ቄስም ሆነ ዲያቆን ሥርዐተ ጥምቀትን ከፈጸመ በኋላ ለአንብሮተ እድ ሐዋርያትን መጠበቅ ግዴታ ነበረበት (የሐዋ ፡ ፰ ፡ ፲፬—፲፯) ፤ ቤተ ክርስቲያን እየተስፋፋች በሄደች ጊዜ ግን ሐዋርያት ተጠማቂዎች ወደ አሉበት ተጠማቂዎችም ሐዋርያት ወደአሉበት ሄደው አንብሮተ እድ ለማድረግና ለመቀበል አስቸጋሪ በመሆኑ በአንብሮተ እድ ፈንታ ሜሮኑን በአንብሮተ እድ ባርከው አጥማቂው ካህን ለተጠማቂው እንዲቀባ ፈቅደዋል ። ስለ ዚህም በዚያው በዘመነ ሐዋርያት በአንብሮተ እድ ስለተተካው ምሥጢረ ቅብዐት (ሜሮን) በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ ይገኛል ፤ (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፤ ፬ ፡ ፴ ፤ ፪ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፩—፳፫ ፤ ፩ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፳—፳፯) ።

## አፈጻጸሙ

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተጠማቂው ሕፃንም ሆነ ሽማግሌ እንደተጠመቀ ሳይውል ሳያድር ሜሮን ይቀባል ፤ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ግን ለሕፃንም ሆነ ለዐዋቂ ሜሮኑን ከጥምቀት ነጥለው በማቆየት ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ይቀባሉ ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ዕድሜ አይወስነውም ፤ በማኅፀን ሳሉ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የተቀበሉ አሉና (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፭) ።

የሜሮን አቀባብ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ግንባርን ብቻ ሳይሆን ከግንባር እስከ እግር የተወሰኑ የአካል ክፍሎች ይቀባሉ ፤ ምሥጢረ ሜሮን የሚፈጸመው ለተጠመቁ ብቻ ነው ፤ (የሐዋ ፡ ፰ ፡ ፲፬—፲፯) ፤ ምሥጢረ ሜሮንን መፈጸም የሚችሉ በመጀመሪያ ሐዋርያት ፤ ቀጥሎ ጳጳሳት ብቻ ነበሩ ፤ በኋላ ግን ሜሮን የማውጣቱ ወይም የማፍላቱ ሥልጣን ለጳጳሳት ሲሆን መቀባት ብቻ ለቀሳውስትም ተፈቅዶአል ፤ ስለዚህ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ቀሳውስትም ሜሮን ይቀባሉ ፤ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ግን አሁንም ቢሆን ምሥጢረ ሜሮንን የሚፈጽሙ ጳጳሳት ብቻ ናቸው ።

## በምሥጢረ ሜሮን የሚገኝ ጸጋ

ተጠማቂው ሜሮን በሚቀባበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ይቀበላል ፤ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በሜሮን ይረጋገጣል ፤ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ዕድገትንና ኃይልን ያገኛል ፤ ለዚህ ሁሉ ምሥጢረ ሜሮን እንደ ማሕተም ነው ፤ (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፴) ።





www.ethiopianorthodox.org

## ፫. ምሥጢረ ቍርባን

ቍርባን ማለት መባዕ ሆኖ የሚቀርብ የሚሰጥ ማለት ነው ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን ስለኃጢአታቸው ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ሁሉ ቍርባንና መሥዋዕት ይባል ነበር ፤ ቍርባን የእህሉ ፡ መሥዋዕት የእንስሳው ነው ፤ በሐዲስ ኪዳን ግን ቍርባን ወይም መሥዋዕት የሚባለው እግዚአብሔር ለሰዎች ያቀረበው ነው ፤ ከዚህም ጋር ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡበት እግዚአብሔርም ወደ ሰዎች የሚቀርብበት መንገድ መሆኑን ቃሉ ያመለክታል ።

ቅዱስ ቍርባን የሚባለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ነው ፤ (፩፡ቆሮ፡ ፲፩፡ ፳፯ ፤) ቅዱስ ቍርባን ፦ መሥዋዕት ተብሎ ይጠራል ። (፩፡ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፯ ፤ ዕብ ፡ ፲፡ ፲፬ ።)

### አመሠራረቱ ፤

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሞቱ አስቀድሞ በጸሎተ ሐሙስ በበዓለ ፋሲካ ቅዱስ ቍርባንን መሥርቶአል ፤ ይህንም ሦስቱ ወንጌላውያን ሁሉ አረጋግጠው ጽፈዋል ፤ (ማቴ ፡ ፳፮፤፳፮—፳፱፤ማር፡ ፲፬፡ ፳፪—፳፭፤ ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፲፱—፳ ፤ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫—፳፭ ።)

ስለ ምሥጢረ ቍርባን በብሉይ ኪዳን ምሳሌ ተመስሎአል፤ ትንቢትም ተነግሮአል ።

ምሳሌው ፡— መልከጼዴቅ ለአብርሃም ያበረከተው ኅብስትና ወይን (ዘፍ ፡ ፲፬ ፡ ፲፰) ፤ በኦሪት ዘሌዋውያን የተዘረዘሩት አምስቱ የመሥዋዕት አይነቶች (ዘሌዋ ምዕራፍ ፩፡ — ምዕራፍ ፯) እስራኤላውያን በነጻነት በዓላቸው በፋሲካ የሠውት የፋሲካ በግ፤ (ዘጸአ ፡ ፲፪ ፤ ፩ ፡ ቆሮ ፡፭ ፡ ፯) ፤ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ለ፵ ዓመታት የተመገቡት መና ዘጸአ ፡፲፮፡ ፲፫—፲፮ ፤ ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፵) የቅዱስ ቍርባን ምሳሌ ነበር ።

ትንቢቱም ፡— በመጽሐፈ ምሳሌ ፱ ፡ ፩—፮ ፤ «ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሰሶችዋን አቆመች ፍሪዳዋን አረደች የወይን ጠጅዋን ደባለቀች ማዕድዋን አዘጋጀች ባሪያዎችዋን ልካ በከተማይቱ ከፍተኛ ሥፍራ ላይ ጠራች ፤ ዕላዋቂ የሆነ ወደዚህ ፈቀቅ ይበል አእምሮ የጎደላቸውንም እንዲህ አለች ፤ ኑ እንጀራዬን ብሉ ፤ የደባለቅሁትንም የወይን ጠጅ ጠጡ ዐላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ» ተብሎ የተነገረውና በሌላም ክፍል ያለው ነው ።



### አፈጻጸሙ

በምሥጢረ ቍርባን አፈጻጸም ጊዜ የሚታዩ ሁለት ምልክቶች አሉ ፤ እነርሱም ኅብስትና ወይን ናቸው ፤ ኅብስቱ ከንጹሕ ስንዴ ይሠራል ፤ ስንዴው ከመጀመሪያ ጀምሮ ኅብስት እስከ ሚሆንበት ድረስ ያለው አሠራር ሁሉ ክርስቶስ ስለእኛ ለተቀበላቸው ጸዋትወ መከራ ምሳሌነት አለው ፤ ወይኑም ከንጹሕ የወይን ፍሬ (ዘቢብ ) ይዘጋጃል ፤ በወይኑና በስንዴው አንዳችም ነገር አይጨመርም ፤ ቤተ ክርስቲያናችን በማናቸውም ቦታ በሚዘጋጅና ልዩ ነገር በተጨመረበት ኅብስትና ወይን ቅዱስ ቍርባን እንዲፈጸም አትፈቅድም ።

ምሥጢረ ቍርባንን መፈጸም የሚችሉ በመጀመሪያ ሐዋርያት ነበሩ (የሐዋ - ፳ ፡ ፯) ፤ ከሐዋርያት በኋላ በእነርሱ እግር የተተኩ ጳጳሳት ምሥጢረ ቍርባንን እንዲፈጽሙ ሆነ ፤ ቤተ ክርስቲያን በየሀገሩ ከተቋቋመች በኋላ ግን ቀሳውስት ምሥጢረ ቍርባንን እንዲያከብሩና እንዲሰጡ ተፈቀደ ፤ ዲያቆናት ግን በአገልግሎት ይላላካሉ ፤ ያስተናብራሉ እንጂ ምሥጢረ ቍርባንን ለመቀደስ ሥልጣን የላቸውም ፤ እርግጥ በዕርፈ መስቀል ደሙን እንዲያቀብሉ ቤተ ክርስቲያናችን ትፈቅዳለች ።

### በምሥጢረ ቍርባን የሚገኝ የማይታይ ጸጋ ፤

በሚታየው በኅብስቱና በወይኑ የማይታየውን የክርስቶስን ሥጋና ደም እንቀበላለን ፤ ስርየተ ኃጢአትን እናገኛለን / (ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮—፳፰) ።

ከክርስቶስ ጋር ኅብረትን እናገኛለን ፤ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶፮ ፡) ከምእመናን ሁሉ ጋርም አንድነት ይኖረናል ፤ (፩፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፯) ፤ በሥጋውና በደሙ የዘለዓለም ሕይወትን እንወርሳለን ፤ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶፬ ፡ ፶፰) ።

### የኅብስቱና የወይኑ መለወጥ ፤

ካህኑ ነቅዕ የሌለበትን ንጹሕ ኅብስት በጻሕል እንደዚሁም የጠራውን ወይን በጽዋዕ አድርጎ ጸሎተ ቅዳሴውን ያደርሳል ፤ ከፍሬ ቅዳሴው መካከል «--- ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ ከመ ትፈኑ ቅዱሰ መንፈሰ ወኀይለ ዲበ ዝንቱ ኅብስት ፤ ወላዕለ ዝንቱ ጽዋዕ ይረስዮ ሥጋሁ ወደሞ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም ፡— የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋውንና ደሙን



www.ethiopianorthodox.org

ያደርገው ዘንድ ቅዱስ መንፈስን ኃይልንም በዚህ ኅብስትና በዚህ ጽዋዕ እንድትልክ አቤቱ እንለምንሀለን፤እንማልድሀለን» የሚለውን ጸሎት በሚ ጸልይበት ጊዜ ፡—በግብረ መንፈስ ቅዱስ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ወይኑም ተለውጦ ደመ አምላክ ይሆናል ፤ (ቅዳሴ ሐዋርያት) ኅብስ ቱና ወይኑ በሚለወጡበት ጊዜ መልካቸውና ጣዕማቸው እንዳለ ነው ፤ መለወጡን የምንመለከተው በእምነት ዓይን ነው ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት ቅዱስ ቍርባን ፣ ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው እንጂ ምሳሌ አይደለም ፤ (ማቴ ፡፳፮፥ ፳፯—፳፰ ፤ ፩፡ቆሮ ፡ ፲፡ ፲፯ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫—፳፯ ፤) እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ የሚያመለክቱት የምንቀበለው ኅብስትና ወይን ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም መሆኑን ነው ፤ ይህን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል መሠረት በማድ ረግ የቤተ ክርቲያን አባቶች ኅብስቱና ወይኑ በካህኑ መሣሪያነት በመን ፈስ ቅዱስ ሥራ በቃለ እግዚአብሔር ተለውጦ የክርስቶስ ሥጋና ደም እንደሚሆን በሰፊው ተናግረዋል ፤ ጽፈዋልም ።

## ምሥጢረ ቍርባንን መቀበል የሚገባቸው ፤

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት መሠረት አምነው የተ ጠመቁ ሥጋውንና ደሙን መቀበል ይችላሉ ፤ ከዚያም በኋላ በየጊዜው ራሳቸውን በንስሐ እየመረመሩ ኃጢአታቸውን በመናዘዝ ቅዱስ ቍር ባንን እንዲቀበሉ ቤተ ክስርቲያናችን ትፈቅዳለች ፤ በንስሐ ሳይዘጋጁ በድፍረት የሚቀበሉ ቢኖሩ ግን ዕዳ እንደሚሆንባቸው ታውጃለች፤(፩፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፰—፳፱፤) ለሕፃናትም ጥምቀት እንደተፈቀደላቸው ሁሉ ቅዱስ ቍርባንንም እንዲቀበሉ ቤተ ክርስቲያናችን ትፈቅዳለች ።

ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ኅብስቱን በወይኑ ጠምተው ያቀብላሉ ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ግን ኅብስቱን በቅድሚያ ፣ ወይኑን በኋላ ታቀብላ ለች ፣ ይህም መድኃኒታችን ለደቀ መዛሙርቱ ካደረገው ሥርዐት ጋር ይመሳሰላል ፤(ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯—፳፰ ።)

# ፬. ምሥጢረ ክህነት

ክህነት ማለት አገልግሎት ማለት ነው ፤ በዚህም መሠረት ካህን ማለት አገልጋይ ማለት ነው ፤ ቃሉ «ኮሄን» ከሚለው ከዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው ።



ምሥጢረ ክህነት ፡— ቃለ እግዚአብሔርን ለማስተማር ምሥጢ ራትን ለመፈጸምና ምእመናንን ለመምራት በጳጳሳት አንብሮተ እድና ጸሎት ለሚገባቸው የሚሰጥ ምሥጢር ነው ፤ ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ለመፈጸም የሚያስችል ይህ ምሥጢረ ክህነት ነው ። (የሐዋ ፡ ፳፡ ፳፰ ።)

## አመሠራረቱ

ምሥጢረ ክህነትን የጀመረ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በሚያርግበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን በአንብሮተ እድ ባርኮ ከዲቁና እስከ ጵጵስና ያለውን ማዕርገ ክህነት ሾሞአቸዋል ፤ (ማቴ. ፳፰ ፡ ፲፱—፳ ፤ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፶ ፤ ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፩—፳፫ ፤ ኤፌ ፣ ፬ ፡ ፲፩—፲፬ ፤) ቀጥሎም ቅዱሳን ሐዋርያት ጳጳሳትን ሾመዋል፤ (የሐዋ፡ ፲፬ ፡ ፳፫ ፤ ፩፡ጢሞ . ፫ ፡ ፳፱ ፤) ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያል ተቋረጠ አንብሮተ እድ በቤተ ክርስቲያናችን አለ ፤ ጳጳሳት መሣሪያ ዎች ናቸው እንጂ ሥልጣኑን በጳጳሳት አድሮ የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነው ።

## የካህናት መዓርጋት

የካህናት መዓርጋት ሦስት ናቸው ፤ እነርሱም ጵጵስና ፣ ቅስናና ዲቁና ናቸው ።

፩/ ጳጳስ ፡— በቤተ ክርስቲያናችን ጵጵስና መሾም የሚችለው ድንግል መነኮስ ነው ፤ በሞት ወይም በበቂ ምክንያት ሚስቱ የተለየችው ካህን ቢመነኩስ ጵጵስና እንዲሾም በቤተ ክርስቲያናችን አይ ፈቀድለትም ፤ ጳጳስ በሁለት ወይም በሦስት ጳጳሳት ሊሾም ይች ላል ፤ ዕድሜው ከ፴ በላይ መሆን አለበት ፤ ጳጳስ የማስተማር ምሥ ጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በሙሉ የመፈጸም ቤተ ክርስቲያንን የመም ራት ሥልጣን በምልዐት አለው፤ (ቲቶ፡ ፩፡ ፭፤) ሜሮን ማፍላት ጽላትና ሌሎች ሐዲሳን ንዋያተ ቅድሳትን ሁሉ የመባረክ ሥልጣን አለው ፤

፪/ ቄስ ፡—እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ዲያቆኑ በዲቁና ሲያገ ለግል ከቆየ በኋላ አግብቶ ወይም መንኩሶ ቅስና ይሾማል ፤ ነገር ግን ቅስና ቅድመ ጋብቻ ወይም ቅድመ ምንኩስና አይፈቀድም ቄስ በአንድ ጳጳስ በአንብሮተ እድ ይሾማል ፤(፩ ፡ ጢሞ. ፫ ፡ ፳፪ ፤



www.ethiopianorthodox.org

የሐዋ. ፲፬ ፡ ፳፫ ፤ ) ቄስ ከመሾሙ በፊት በቲቶ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡ እንደ ተጻፈው መሆን አለበት ።

ቄስ የማስተማር ምሥጢራትን የመፈጸምና ምእመናንን የመምራት ሥልጣን ከጳጳሱ ይቀበላል ፤ ነገር ግን ሜሮን አያፈላም ክህነት አይሰጥም፤ ታቦት ፡ አዲስ ቤት ክርስቲያንና መንበር አይባርክም ።

፫/ ዲያቆን ፦ ዲያቆን ከመሾሙ በፊት በ፩ ፡ ጢሞ. ፫ ፡ ፰—፲፫ እን ደተጻፈው ሆኖ መገኘት እንዳለበት ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች ፤ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ዲያቆን ቅድመ ጋብቻ ይሾማል ፤ በአንድ ጳጳስ በአንብሮተ እድ ይሾማል ፤ (የሐዋ. ፮ ፡ ፮) ሹመቱም ጳጳሱ ንና ቄሱን ለመርዳት ብቻ ነው ፤ ዲያቆን ምሥጢራትን መፈጸም አይ ችልም ፤ ነገር ግን ማንበብ ማስተማርና መስበክ ለዲያቆናት ይፈቀድ ላቸዋል ። (የሐዋ ፡ ፮ ፡ ፫—፮) ።

በ፩፡ ጴጥሮስ ፪ ፡ ፱—፲ ላይ ያለውን ቃል በመመልከት ክህነት ለሁ ሉም ማለት በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ ለወንዶችም ለሴቶችም ይገባቸዋል፤ የሚሉ አሉ ፤ ይህንም የመሰለ ቃል በብሉይ ኪዳን በኦሪት ዘጸአት ፲፱ ፡ ፮ ፡ ላይ ይገኛል ፤ ይሁን እንጂ በዚያ ጊዜም እስራኤላውያን ሁሉ ካህናት አልነበሩም ፤ የብሉይ ኪዳን ካህናት የተለዩ ነበሩ ፤ ክህነት ይገባናል ብለው በድፍረት የተነሡ ቢኖሩም ተቀጥተዋል (፪፡ዜና ፡ ፳፮ ፡ ፲፮ ፤ ዘኁል. ፲፮)፤ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ቃል የሚያመለክተው መሥዋ ዕተ ስብሐት ለማቅረብ የሚያስችለውን ሀብት መንፈሳዊ ነው እንጂ በጅምላ ሁሉም ከዲቁና እስከ ጵጵስና ማዕርግ አላቸው ለማለት አይደ ለም ፤ ጌታችንም በተለይ ለሐዋርያት የሰጠውን ሥልጣን ለተከታዮቹ ሁሉ አልሰጠም ፤ (ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፲፪—፲፫ ፤ ማቴ ፤ ፲፰ ፡ ፲፰ ) ።

## ፭ ምሥጢረ ንስሓ

ንስሓ መጸጸት ከኃጢአት መመለስ ፡ ራስን ማደስና መለወጥ ማለት ነው ፤ ንስሓ ተነሳሒው በአናዛዡ ካህን በኩል ከራሱ ከእግዚአብሔር በእውነተኛ ኀዘን ሥርየተ ኃጢአትን የሚቀበልበት ምሥጢር ነው ።

ከአዳም የተወለደ ሁሉ ከአዳም በተወረሰው የኃጢአት ዘርዕ ምክ ንያት የኃጢአት ዝንባሌ አለበት ፤ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል «- - - እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ ፤ - - - የማልወደውን የማደርግ ከሆንኩ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደ ለሁም በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ» (ሮሜ ፡ ፯፡ ፲፭—፲፰ )፤



ስለዚህ ሰው ከጥምቀት በፊት የሠራው ኃጢአት ሁሉ በጥምቀት ይሰ ረይለታል ፤ ከጥምቀት በኋላ የሠራው ኃጢአት ግን በንስሓ ይሰረይለት ዘንድ እግዚአብሔር ምሥጢረ ንስሓን ለሰው ልጆች ሰጥቶአል ።

### አመሠራረቱ

ምሥጢረ ንስሓን የመሠረተ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ከት ንሣኤው በኋላ ሥልጣነ ክህነትንለሐዋርያት በሰጣቸው ጊዜ ምሥጢረ ንስ ሓን መሥርቶአል(ዮሐ፡፳፡፳፩—፳፫)፤ ከዚያም አስቀድሞ ኃጢአተኛውን ከኃጢአቱ መፍታትና ማሠር እንደሚችሉ በነገራቸው ጊዜ የምሥጢረ ንስሓን ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር (ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ፤ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰)፤ በመ ሠረቱ ኃጢአትን የማስተስረይ ኃይል ለጌታችን ብቻ ነው (ሉቃ ፡ ፭ ፡ ፳) ፤ ነገር ግን ይህን ኃይል ራሱ ጌታችን ለሐዋርያት ሰጣቸው ፤ በሐዋር ያትም በኩል ለጳጳሳትና ለቀሳውስት ተሰጣቸው (ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፩—፳፫)።

### አፈጻጸሙ

ምሥጢረ ንስሓን መፈጸም የሚችሉ ጳጳሳትና ቀሳውስት ብቻ ናቸው ፤ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ተነሳሒውና ካህኑ ብቻቸ ውን ሆነው ይፈጸማል ፤ ተነሣሒው ማለት ኃጢአተኛው ስለሠራው ኃጢአት ከፍተኛ ጸጸት ፡ ልባዊ ኑዛዜ መናዘዝ ፤ ወደ ሠራው ኃጢአት እንደገና ላይመለስ መወሰን በክርስቶስ ጽኑዕ እምነት በምሕረቱም ፍጹም ተስፋ ማድረግ አለበት ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ኃጢአትን ለካህን አምኖ መናዘዝ ያስፈልጋል ፤ ካህኑም ኑዛዜውን በምሥጢር መጠበቅ አለበት ፤ ኑዛዜ ራስን በካህኑ ፊት መከሰስና መውቀስ ማለት ነው ፤ ኑዛዜ ኃጢአተኛውን በሠራው ኃጢአት እንዲገሥጽ እንዳይመለስበትና እንዲያ ፍርበት ያደርገዋል ፤ ስለ ኑዛዜ መጻሕፍት ቅዱሳት በሰፊው ይናገራሉ ፤ (የሐዋ ፡ ፲፱፡ ፲፰ ፤ ያዕ ፡ ፭፡ ፲፮ ፤ ፩፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፱ ) ፤ ንስሓ መግባት የሚገባው ኃጢአትን በተገነዘበ ጊዜና ቅዱስ ቊርባን ከመቀበል በፊት ነው ።

### በምሥጢረ ንስሓ የሚገኝ ጸጋ

ተነሳሒው በመምህረ ንስሓው ፊት ቀርቦ ኃጢአቱን በሚገባ ከተ ናዘዘ በኃጢአቱ ካለቀሰ ስርየተ ኃጢአትን ያገኛል ፤ ከእግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

ጋር ይታረቃል ፤ የነፍስ ሰላምንና ዕረፍትን ያገኛል ፤ በድሎ የነበረው እንዳልበደለ ይሆናል ፤ ፍጹም ተሐድሶና ለውጥን ያገኛል ።

### ካህኑ ለተነሳሒው የሚሰጠው ቅጣት (ቀኖና)

ተነሳሒው የኃጢአቱን ክብደት እንዲያስታውስ ካህኑ፡ —ጾም ለተወሰነ ጊዜ እንዲጾም እንዲጸልይ ምጽዋት እንዲሰጥ ከምሥጢራት እንዲከለከል ያዝዘዋል ፤ ይህም በጌታችንና በሐዋርያት ታዝዞአል ፤ (ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ፤ ፩ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፩—፭) ።

ይህ የሚሆንበት ምክንያት ተነሳሒው ኃጢአቱ ምን ያህል አሳዛኝና ከባድ መሆኑን እንዲረዳ ፡ ነፍሱን ለማንጻት እንዲችል ሌሎች ቅጣት መቀበሉንና መመለሱን ተመልክተው እንዲቀበሉት ፤ (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፮—፰ ፤) እርሱንም አይተው እንዲገሠጹ (፩፡ ጢሞ፡ ፭ ፡ ፳ ፡ ) ነው ።

## ፮. ምሥጢረ ተክሊል

ተክሊል የሚለው ቃል ለሙሽሮች በጋብቻቸው ጊዜ የሚፈጸመውን ሥርዐት ፡ ቃል ኪዳንና የሚቀዳጁትን አክሊል የሚለብሱትንም ልብሰ መርዓ የሚያመለክት ነው ፤ ምሥጢረ ተክሊል ሙሽራውንና ሙሽሪትን አንድ የሚያደርግ መለኮታዊ ጸጋን የሚያሰጥ የጋብቻን አንድነት የሚያጸና ምሥጢር ነው ፤ ጋብቻ ወይም ምሥጢረ ተክሊል ከሌሎች ምሥጢራት ተለይቶ ምሥጢራዊና ተፈጥሮታዊ ነው ፤ ምሥጢራዊ መባሉ ጸጋ እግዚአብሔር ስለሚሰጥበት ነው ፤ ተፈጥሮታዊ መባሉም ማንም በተፈጥሮ ባሕርዩ ስለ ሚፈጽመው ነው ።

### አመሠራረቱ

እግዚአብሔር በጥንተ ፍጥረት የመጀመሪያውን ሰው በፈጠረ ጊዜ «ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም ረዳትን እንፍጠርለት እንጂ» ብሎ ሔዋንን በመፍጠሩ ቅዱስ ጋብቻን መሥርቶአል ፤ (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲፰—፳፬ ፤) ቀጥሎም «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዓት - » በማለት የሁለቱን አንድነት ባረከ ፤ ( ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፰ ። )

ነገር ግን ይህ አንድነት በኃጢአት ምክንያት ረክሶ ስለነበር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደገና ታደሰ ፤ ራሱ ጌታችን በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ተገኝቶ ውሃውን ወደ ወይን በመለወጥ ጋብቻን አከበረ ፤ (ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፩—፲፩) ።



### የጋብቻ ዓላማ

ሀ. የሰው ዘርዕ እንዳይቋረጥ ዘርዕ ለመተካትና ምድርን ለመሙላት ነው ፤ (ዘፍ፡ ፩ ፡ ፳፯—፳፰ ፤) በዚህም ዓላማው ጋብቻ የእግዚአብሔር የሥራው ኅብረት ነው ፤ ጋብቻ ለማኅበረ ሰብእ (ለሀገር) ለመንግሥተ እግዚአብሔር አስፈላጊ ነው ፤ ጋብቻን መቃወም ራስን ኅብረተ ሰብእን እግዚአብሔርንም መቃወም ነው ።

ለ. የባሕርይ ፍትወትን ለማራቅ ነው ፤ (፩፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፰—፱ ፤ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ፤)

ሐ. ሰው ብቻውን መኖር ስለማይገባው ፡ እርስ በርስ በመረዳዳት ለመኖር ነው ፤ (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።)

### አፈጻጸሙ

ምሥጢረ ተክሊል በቤተ ክርስቲያን እንጂ በሌላ ቦታ አይፈጸምም ፤ በቄስ ወይም በጳጳስ ይፈጸማል ፤ ተክሊል በድንግልና ኖረው ለሚጋቡ እንጂ ለፈቶች አይደረግም ፤ በክርስትና ሃይማኖት ሥርዐት ፡ ጋብቻ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት አንዲት ሴት ለአንዲት ወንድ እንጂ ብዙ ሴቶች ለአንድ ወንድ ብዙ ወንዶችም ለአንዲት ሴት አይፈቀድም ፤ ስለዚህ ከአንዲት ሴት በላይ ወይም ከአንድ ወንድ በላይ ለሚያገቡ ምሥጢረ ተክሊል አይፈጸምም ።

### የተጋቢዎች ግዴታ

የሚጋቡት ሁለቱም የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላት መሆን አለባቸው ፤ ጋብቻን የሚከለክል ሥጋዊና መንፈሳዊ ዝምድና የአካልና የአእምሮ ጉድለት ከመጠን በላይ የሆነ የዕድሜ መበላለጥ መኖር የለበትም ፤ የወላጆች ፈቃድ ብቻ ሳይሆን የተጋቢዎቹም ፈቃድ እንዲሆን ያስፈልጋል ።

### በምሥጢረ ተክሊል የሚገኝ ጸጋ

ምሥጢረ ተክሊል የሙሽራውንና የሙሽራይቱን ባሕርያዊ አንድነት ወደ ንጹሕ መንፈሳዊ አንድነት ይለውጣል ፤ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ጋብቻ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያኑ አንድነት ምሳሌ ነው ፤ በመሆኑም የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን አንድነት ለዘለዓለም እን



www.ethiopianorthodox.org

ደሆን ባልና ሚስት ሳይለያዩ እንዲኖሩ የሚያስችል መንፈሳዊ ኃይልንና አንድነትን በምሥጢረ ተክሊል ያገኛሉ ፤ (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፭ ።)

ጋብቻ ከሁለቱ አንዱ ካልሞተ ወይም አመንዝራ ካልሆነ በቀር አይፈርስም ፤ «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለይ አይገባ ውም ። (ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፩—፫ ፤ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፮ ፤)

## ፯ ምሥጢረ ቀንዲል

ምሥጢረ ቀንዲል የታመሙ ምእመናን በቅብዐ ቅዱስና በቀሳው ስት ጸሎት ለነፍና ለሥጋ ፈውስ የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚቀበሉበት ምሥጢር ነው ።

ቀንዲል መብራት ማለት ነው ፤ ምሥጢረ ቀንዲል በሚደረግበት ጊዜ ሰባት መብራት ይበራል ፤ ስለዚህ ስያሜው ከሥርዐቱ አፈጻጸም ተወስዶአል ፤ ከዚህም ጋር የጥንት ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበት መብራት የዘይት ቅብዐት ነውና ቅብዓ ዘይቱ በግብሩ ቀንዲል ተብሎአል ።

### አመሠራረቱ ፤

ከትንሣኤ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን በላ ካቸው ጊዜ ድውይ የመፈወስን ኃይል ሰጥቶአቸዋል ፤ (ማር፡፲፮፡፲፯—፲፰፤) ከዚያም በፊት በጥንተ ስብከት ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ በየከተማው በላካቸው ጊዜ ድውያንን በዘይት እየቀቡ ይፈውሱ ነበር ፤ (ማር፡ ፮፡ ፲፫ ።) ከዚያ በኋላ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥጢሩ መጋቢዎች ፤ እን ደመሆናቸው በትእዛዙ መሠረት ሲሠሩበት ኖረዋል ፤ (፩፡ ቆሮ፡፬፡ ፩፤) ቀጥሎም ቀሳውስት በዘይት እየቀቡና እየጸለዩ ሕሙማንን እንዲፈውሱ ሐዋርያት አዝዘዋል ፤ (ያዕ፡ ፭፡ ፲፬—፳ ፤) እስካሁንም ድረስ ከሐዋርያት ሲያያዝ በመጣው ትውፊት መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን በምሥጢረ ቀንዲል ትገለገላለች ።

### አፈጻጸሙ ፤

ምሥጢረ ቀንዲል የሚፈጸመው በንጹሕ የወይራ ዘይት ነው ፤ ቅብዐ ዘይቱ በጳጳስ ይባረካል ፤ በቄስም ሊባረክ ይችላል ፤ ምሥጢረ ቀንዲል በጳ ጳስ ወይም በቄስ በቤተ ክርስቲያን ወይም በመኖሪያ ቤትና በሆስፒታል ሊፈጸም ይችላል ፤ በሽተኛው ከመቀባቱ በፊት ኃጢአቱን ይናዘዛል ።



### በምሥጢረ ቀንዲል የሚገኝ ጸጋ ፤

በሽተኛው ቀንዲል ሲቀባ በሥጋዊ ደዌ ደክሞ የነበረው መንፈሳዊ ኃይሉ ይበረታል ፤ ሥጋና መንፈስ አንድ ስለሆኑ የአንዱ ሌላውን ይሰ ማዋል፤ ሥጋ ቢደክም መንፈስም ይደክማል ፤ መንፈስ ሲጠነክር ደግሞ ሥጋም ይጠነክራል ፤ የመንፈስ ኃይል የሥጋን ድካም ያስወግዳል ፤ ከዚህም ጋር በምሥጢረ ቀንዲል በሽተኛው ስርየተ ኃጢአትን ያገ ኛል ፤ ይህም ኑዛዜ ሲጨመርበት ነው ።

አንዳንድ ሊቃውንት «ምሥጢረ ቀንዲል የሚፈጸመው ለሥጋዊ ፈውስ ከሆነ ምሥጢር መባል የለበትም» ይላሉ ምክንያታቸውንም ሲሰጡ ምሥጢር መባል የሚገባው መንፈሳዊውን ጸጋ ብቻ የሚያስ ጠው ነው ይላሉ ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ግን ምሥጢረ ቀንዲል ለሥጋም ለነፍስም ፈውስ የሚገኝበት ምሥጢር መሆኑን ታምናለች ።

ምሥጢረ ቀንዲል ለሞት መዘጋጃ እንደሆነ የሚያምኑ አሉ ፤ እን ደዚህ የሚሉ ክፍሎች ምሥጢረ ቀንዲል በሽተኛው ሊሞት ሲያጣጥር ይፈጽሙለታል ፤ እንደነርሱ ሥርዐት ምሥጢረ ቀንዲል የሚፈጸመው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ምሥጢረ ቀንዲል ለደዌ ሥጋም ለደዌ ነፍስም እንደሚበጅ ታምናለች ፤ ስለዚህም ምእመናን በታመሙ ጊዜ ሁሉ ምሥጢረ ቀንዲልን ትፈጽምላቸዋለች ።

ምሥጢረ ቀንዲል በ፩፡ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፰ ላይ ከተጠቀሰው ሀብተ ፈውስ የተለየ ነው ፤ ማንኛውም ጳጳስ ወይም ቄስ ምሥጢረ ቀንዲልን ለመፈ ጸም ሥልጣን አለው ፤ «ሀብተ ፈውስ» የሚባለው ግን ለተለዩ ሰዎች ነው ፤ የተለዩ ከተባለም ለካህን ወይም ካህን ላልሆነ ሊሰጥ ይችላል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ፲፫ | ትንሣኤ ሙታን የክርስቶስ ዳግም ምጽአትና

## የመጨረሻው ፍርድ ።

የዚህ ዓለም ፍጻሜ በሚሆንበት ጊዜ በተከታታይ የሚፈጸሙ ነገሮች አሉ ፤ እነርሱም የሙታን ትንሣኤ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የመጨረሻው ፍርድና የዘለዓለም ሕይወት ናቸው ፤ እነዚህም ነገሮች በቅዱሳት መጻሕፍት በሃይማኖት ቀኖና በትምህርተ አበውም ተረጋግጠው ተነግረዋል ።

### ፩/ ትንሣኤ ሙታን

ሞት የሰው ፍጻሜ አይደለም ፤ ከጊዜያዊ ሕይወት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት መሸጋገሪያ ነው እንጂ ፤ ዛሬ ፈርሶ በስብሶ ዐፈር ሆኖ ያለው የሰው ሥጋ ከነፍስ ጋር ተዋሕዶ ይነሣል ፤ ቀድሞ ሥጋን ከመሬት ወስዶ ነፍስንም እምኀበ አልቦ አምጥቶ አዋሕዶ ሰውን የፈጠረ አምላክ ኋላ ነፍስን ካለችበት ሥጋንም ከመቃብር እንደገና ሰብስቦ ሕይወት ሰጥቶ ማንሣት አይሳነውምና ።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ሕያዊት (የማትሞት) ነፍስን ሲሰጣቸው ሥጋቸውም የማይሞት ነበር ፤ ነገር ግን በሰይጣን ምክር በኃጢአት በወደቁ ጊዜ ሞት ተፈረደባቸው ፤ ይሁን እንጂ ሰው በሕይወት እንዲኖር የነበረው የእግዚአብሔር ዓላማ በሰይጣን አልተደመሰሰም ፤ ሰው ከሞተ በኋላ ተነሥቶ ለዘለዓለም እንዲኖር እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ትንሣኤ ዘጉባኤን መደበ ።

ስለዚህ የዛሬው ሕይወት ጊዜያዊ ነው ሞትም ጊዜያዊ ነው በመጨረሻ ጊዜ ዘለዓለማዊ ሕይወት ብቻ ይኖራል ።

ሥጋ አሁን ባለው መልኩ አይነሣም ትንሣኤ በተሐድሶ ነውና ጉድለት ያለበት አካል ሁሉ በጉድለቱ አይነሣም በትንሣኤ ጊዜ ረዥም ና አጭር ቀይና ጥቁር አይኖርም፤ዛሬ ያለው የሥጋ ፍላጎት ሁሉ ያንጊዜ አይኖርም ፤ ማግባት መጋባት አይኖርም ፤ ከትንሣኤ በኋላ ሰዎች ሁሉ እንደ መላእክት ሆነው ይኖራሉ ፤ ( ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴ ፤) ዛሬ ነፍስ በሥጋ እንዳለች ሁሉ ኋላ ሥጋ በነፍስ ይኖራል ።

ትንሣኤው በተሐድሶ ቢሆንም የሚነሣው ያው ቀድሞ የነበረው አካል ነው ፤ ዛሬ መልካም ሥራ ያልሠራ ሌላ አካል ተነሥቶ ዋጋ አይቀበልም ፤ እንደዚሁም ዛሬ ክፉ ያልሠራ ሌላ አዲስ አካል ተነሥቶ ቅጣት አይቀበልም ፤ ስለዚህ መልካምም ሆነ ክፉ ሥራ የሠራው አካል ይነሣል ፤

ትንሣኤ ሙታን በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት ተረጋግጦ ተነግሮአል ። (ኢሳ፡ ፳፮ ፡ ፫ ፡ ዳን፡ ፲፪ ፡ ፪፥) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ሙታንን በራሱ ትንሣኤ አረጋግጦአል ፤ (ሮሜ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ፡) በቃሉም ትንሣኤ ሙታንን አጽድቆ ተናግሮአል፤ (ዮሐ፡ ፭፡ ፳፰—፳፱ ፡ ፮ ፡ ፴፱ ፤ ፵—፵፬ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬—፳፭ ፤) ሐዋርያትም ትንሣኤ ሙታንን ሰብከዋል ፤ (የሐዋ. ፬. ፩. ፤ ፩. ቆሮ. ፲፭. ፩. ተሰ. ፬. ፲፫.—፲፯. ፤ ራእ. ፳ ፡ ፲፫ ፤ የሃይማኖታችንም ቀኖና የመጨረሻው ክፍል «ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን የሙታንን ትንሣኤ ተስፋ እናደርጋለን» በማለት የሰው ልጅ ዋና ተስፋው ከሞት በኋላ ሕይወት ከመቃብር ባሻገር ትንሣኤ መኖሩን ማመን እንደሆነ ያስረዳል ።

### የትንሣኤ ዓይነት ፤

የሰው ዘር ሁሉ በምንም ዓይነት ሞት ቢሞት ይነሣል ፤ ሙታን ሁሉ ክርስቶስ እንደተነሣ ይነሣሉ ፤ (ሮሜ፡ ፮ ፡ ፳፫ ፤ ፩ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፫—፳ ፤) ጻድቃንም ኃጥአንም ይነሣሉ ፤ (ማቴ፡ ፳፭፡ ፴፩—፵፮፤) ሁሉም መለከት በተነፋ ጊዜ ይነሣሉ ፤ (፩ ቆሮ. ፲፭ ፡ ፶፪ ፤ ፩ ተሰ. ፬ ፡ ፲፮፤) ነገር ግን ትንሣኤው የተለያየ ነው ፤ የጻድቃን ትንሣኤ የክብር ነው ፤ የኃጥአን ትንሣኤ ግን የሃሳር ነው፤( ዮሐ. ፭. ፳፰—፳፱፤)ጻድቃን ፈጣሪያቸው ክርስቶስን መስለው ይነሣሉ ፤ ኃጥአን ግን አለቃቸው ሰይጣንን መስለው ይነሣሉ ።

### የትንሣኤ ጊዜ

ትንሣኤ ሙታን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ይሆናል ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤና ዳግም ምጽአት የተያያዙ ናቸው ፤ በመካከል የሚሆን ሌላ ጣልቃ ነገር አይኖርም ።

ትንሣኤ ሙታን አንድ ጊዜ ነው ፤ ስለዚህም ራሱ ጌታችን በመከር መስሎ አስተምሮአል ፤ መከሩ አንድ ጊዜ እንደሆነ ትንሣኤ ሙታንም አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል ፤ በሕይወት የሚቆዩት ግን ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ወዲያውኑ ይለወጣሉ ፤ (፩ ተሰ. ፬ ፡ ፲፮—፲፯፤) ከትንሣኤ ሙታን ቀጥሎ ወዲያው ጌታችን ይመጣና የመጨረሻ ፍርድ ይሰጣል ፤ ከዚያም የዓለም ፍጻሜ ይሆናል ።





www.ethiopianorthodox.org

## ፪/ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ፤

ቀድሞ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ በትሕትና መጥቶ የነበረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ፍጻሜ ጊዜ ዳግመኛ በክብር ይመጣል ፤ ዳግም ምጽአቱ ከቀዳማዊ ምጽአቱ ይለያል ፤ ቀዳማዊ ምጽአቱ በትሕትና ነበር ፤ ዳግም ምጽአቱ ግን በግርማ ይሆናል ፤ ቀዳማዊ ምጽአቱ «ነስሑ» እያለ ለማስተማር ነበር ፤ ዳግም ምጽአቱ «ሑሩ» ና «ንዑ» ብሎ ለመ ፍረድ ይሆናል ።

የክርስቶስ ቀዳማዊ ምጽአቱ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ተነግሮ እንደ ነበር ዳግም ምጽአቱም በሐዲስ ኪዳን ተነግሮአል ።

ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዳግም ምጽአቱ ደጋግሞ ተና ግሮአል . (ማቴ፡ ፳፬ . ፴ ፤ ፳፭ . ፲፴ ፤ ፳፮ . ፷፬ ፤ ዮሐ. ፲፬ . ፫ .) መላእክ ትም «ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል» በማለት ዳግመኛ ተመልሶ መምጣቱን በግልጥ አስረድተዋል ፤ (የሐዋ፡ ፩ . ፲፩፤) ቅዱስ ጳውሎስና ሌሎች መልእ ክታትን የጻፉ ሐዋርያትም ስለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሰፋ አድርገው ጽፈዋል፤ (፩.ተሰ.፬. ፲፭—፲፯፤ ፪፡ ተሰ.፩፡፯—፰ ፤ ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፫፤ ፩፡ ቆሮ . ፩ ፡ ፰ ፤ ዕብ ፱ ፡ ፳፰ ፤ ፩፡ ጴጥ . ፩ ፡ ፲፯ ፤ ፩ ዮሐ . ፪ ፡ ፳፰ ፤ ያዕ . ፭ ፡ ፯ ፤ ይሁዳ ፡ ፲፬ )፤ በሃይማኖታችንም ቀኖና «በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ዳግመኛ በክብር ይመጣል» በተባለው መሠረት ምጽአቱ ዘወትር ሲታሰብ ይኖራል ፤ በጸሎተ ቅዳሴም «ሞትህንና ቅድስት ትንሣኤህን ዳግመኛ መምጣትህንም እንናገራለን» እያለች ቅድስት ቤተ ክርስቲያ ናችን ሁልጊዜ ታውጃለች ።

### የዳግም ምጽአቱ ምልክቶች

ጌታችን ዳግመኛ ከመምጣቱ በፊት መምጣቱ የተቃረበ መሆኑን የሚገልጡ ምልክቶች በዓለም እንደሚታዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገ ራሉ ፤ ምልክቶች እንደ ሬታውራሪ ሆነው መምጣቱን ያሳውቃሉ ፤ ከምልክቶቹ አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ. ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል ፤(ማቴ . ፳፬ ፡ ፲፬፤ ማር . ፲፫ ፡ ፲)፤

ለ. እስራኤላውያን ሁሉ ለመዳን ያምናሉ ፤(ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ )።

ሐ. ሐሳዊ መሢሕ በሐሳውያን ነቢያትና መሢሓን አድሮ በሰ ይጣን ኃይል ታአምራት እያደረገ ይመጣል ፤ ሕዝብን ያስ ታል ፤ ማቴ . ፳፬ ፡ ፭—፲፩ ፤ ፪፡ ተሰ . ፪ ፡ ፫—፬ ፤ ፩ ዮሐ . ፪ ፡ ፲፰—፳፪ ።



መ. ዓመፅ ይበዛል ፍቅር ይቀዘቅዛል፤ (ማቴ . ፳፬፡ ፲፪፤) ከዚያ በፊት ያልሆነ ወደፊትም የማይሆን ታላቅ መከራና ሁከት ይሆናል ፤ (ማቴ . ፳፬ ፡ ፳፩፤) ረኃብ ጦርነት ፍርኃትና ሽብር የመሬትና የሰማያት መናወጥ ይሆናል ፤ (ማቴ . ፳፬ ፡ ፳፱—፴፩ ፤ ማር. ፲፫ ፡ ፳፬—፳፭ ፤ ሉቃ. ፳፩፡ ፳፭—፳፮) ፤ ፀሐይና ጨረቃ ይጨል ማሉ ከዋክብት ይረግፋሉ በሰማይ ላይ ምልክት ይታያል ፤ (ማቴ፡ ፳፬ ፡ ፳፱—፴)፤ በመጨረሻ ጊዜ በሰማይ ላይ የሚታየው ምልክት መስቀል እንደሚሆን የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት ይተ ረጕማሉ ፤ ከእነዚህ ምልክቶች ሁሉ በኋላ ክርስቶስ በደመና መጥቶ ይታያል ።

### የመምጣቱ ጊዜ

ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመጣበት ዓመትና ወር ዕለትና ሰዓት ፈጽሞ አይታወቅም ቅዱሳት መጻሕፍትም ስለዚህ አይነግሩንም ፤ ጊዜው ሲደርስ እንደ ሚሆን ከማመንና ተዘጋጅቶ ከመጠበቅ በቀር የመምጣቱ ዘመንና ወራት ፤ ዕለትና ሰዓት ነገር ምሥጢር ነው ፤ ከአብ በቀር ማንም አያውቀ ውም መላእክት አያውቁትም (ማቴ. ፳፬ ፡ ፴፮ ፤ ማር. ፲፫፡ ፴፪ )፤ የሰው ልጅ ችም ማለት ሐዋርያትም አያውቁትም (የሐዋ ፩ ፡ ፯) ።

ነገር ግን ጊዜው የተቃረበ መሆኑ ተገልጦአል ፤ ይህም ማለት ቢዘ ገይም እንኳ የማይቀር መሆኑን ያስረዳል ፤ (ዕብ.፲ ፡ ፳፭ ፤ ያዕ. ፭ ፡ ፱ ፤ ፩ ፡ ጴጥ. ፬ ፡ ፭) ።

### የአመጣጡ ሁኔታ ፤

ጌታችን በሚመጣበት ጊዜ ሁሉም እንዲያየው በክበበ ትስብእት ይመጣል ፤(ማቴ. ፳፬፡ ፴ ፤ የሐዋ.፩ ፡ ፲፩ ፤ ቲቶ ፪ ፡ ፲፫ )፤ ሊቃነ መላእክት የመምጣቱን ዐዋጅ በመለከት ያሰማሉ ፤ (፩ ፡ ተሰ ፬ ፡ ፲፮)፤ ሠራዊተ መላእ ክት አጅበውት ይመጣሉ፤ (፪፡ ተሰ. ፩፡ ፯) ፤ የተሰቀለበት መስቀል በሰማይ ላይ ይታያል ፤ (ማቴ.፳፬ ፡ ፴)፤የሰው ልጅ ምልክት የተባለ መስቀል ነውና ።

### የመምጣቱ ዓላማ ፤

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የቀዳማዊ ምጽአቱ ዓላማ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ ወንጌልን አስተምሮ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሙቶ ተነሥቶ



www.ethiopianorthodox.org

ሰውን በኃጢአት ምክንያት ከመጣበት የሞት ፍርድ ለማዳን ነበር ፤ ነገር ግን ዳግመኛ የመምጣቱ ዓላማ «በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ» ይሆናል ፤ ከትንሣኤ ዘጉባኤ በኋላ ክርስቶስ በክብር ተገልጦ ሁሉም እያዩት በገሀድ ይፈርዳል ፤ (ማቴ ፳፭ ፡ ፴፩=፵፮) ።

ዛሬ በሞት ጊዜ ያለው ፍርድ ጊዜያዊ ከመሆኑም በላይ ግላዊ ነው ፤ ፍርድ ከሚቀበለው ግለሰብና ከእግዚአብሔር በቀር በመካከል የሚያይ ሌላ የለም ፤ በመጨረሻው ቀን ግን እያንዳንዱ ሰው በዐደባባይ በሁሉም ፊት ይፈረድበታል ፤ ይህም የሚሆነው አንዱ ሌላውን ምን ያህል እንደበደለ ያውቅ ዘንድ ነው ፤ (ራእ ፡ ፳ ፡ ፲፪) ።

በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ቀድሞ በዚህ ዓለም በሥጋ የጀመረው የአድኅኖት ሥራ የቤተ ክርስቲያንም ክብር በምልዐት ይፈጸማል ፤ ምክንያቱም ዛሬ በሃይማኖተ ወንጌል በምግባረ ወንጌል ጸንተው የኖሩ ጻድቃን በዳግም ምጽአቱ ጊዜ «ንዑ ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ ሰማያት የአባቴ ቡሩካን መንግሥተ ሰማያትን ትወርሱ ዘንድ ወደ እኔ ኑ» ተብለው ወደ ዘለዓለም የደስታ ሕይወት ይሄዳሉ ፤ በዚያም ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን እያዩ በክብር ይኖራሉ ፤ ነገር ግን ክብራቸው እንደ ሥራቸው ይለያያል ፤ (፩ ቆሮ ፲፭ ፡ ፵—፵፩) ።

ዛሬ ከሃይማኖተ ወንጌል ከምግባረ ወንጌል ወጥተው የኖሩ ኃጥአን ደግሞ «ሑሩ እምኔየ ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓለም እናንተ የተረገማችሁ ከእኔ ተለይታችሁ ወደ ዘለዓለም እሳት ሂዱ» የሚል ፍርድ ተፈርዶባቸው በማያቋርጥ የቅጣት ሕይወት ይኖራሉ ፤ (ማቴ.፳፭ ፡ ፴፩=፵፮ ፤ የሐዋ. ፲፯፡፴፩ ፤ ፡ሮሜ ፪ ፡ ፲—፲፯) ።

በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ሞት ይጠፋል ፤ ሰይጣንም ለዘለዓለም ይታሠራል ፤ ሕይወት ብቻ ለዘለዓለም ይቀጥላል (፩ ቆሮ. ፲፭ ፡ ፶፩—፶፯ ዕብ.፪ ፡ ፲፬ ፤ ራእ. ፳ ፡ ፲—፲፭ ፡ ፳፪ ፡ ፲፪) ።



www.ethiopianorthodox.org